# በገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ሚኒስቴር

## የማዕከላዊ ስታቲስቲክስ ኤጀንሲ

# የ1998 በጀት ዓመት የዘጠኝ ወራት

# ዕቅድ አፈጻጸም ግምገማ ሪፖርት


ሚያዝያ 1998

አዲስ አበባ

# በገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ሚኒስቴር
# የማዕከላዊ ስታቲስቲክስ ኤጀንሲ

# የ1998 በጀት ዓመት የዘጠኝ ወራት
# ዕቅድ አፈጻጸም ግምገማ ሪፖርት

ሚያዝያ 1998

አዲስ አበባ

# ማውጫ

አርዕስት ገጽ


1. መግቢያ ....1
2. የኢኮኖሚክ ስታቲስቲክስ ....3
   2.1 የተፈጥሮ ሃብትና ግብርና ስታቲስቲክስ ጥናት ....3
   2.2 የቤተሰብ በጀትና ዋጋዎች ስታቲስቲክስ ጥናት ....7
   2.3 የኢንዱስትሪ፣ንግድ፣ ትራንስፖርትና መገናኛ ስታቲስቲክስ ጥናት ....12
3. የሥነ - ሕዝብ ስታቲስቲክስ ....14
   3.1 የማህበራዊ ስታቲስቲክስ ጥናት ....14
   3.2 የሕዝብና ቤት ቆጠራ የቅድመ ዝግጅት ዝግጅት ሥራዎች ....17
4. የ1998 በጀት ዓመት የፊዚካል ሥራ አፈጻጸም ....24
5. ሳምፕሊንግ ሜቶዶሎጂን በተመለከተ ....26
6. መረጃ ማቀነባበርን በተመለከተ ....30
7. የኢንፎርሜሽን ኮሙኒኬሽን ....31
8. የሲቪል ሰርቪስ ማሻሻያ ጽ/ቤት ዝግጅትን በተመለከተ ....33
9. የማስታወቂያና ሕዝብ ግንኙነት አገልግሎት ....35
10. የኦዲት አገልግሎት ....37
11. የሕግ አገልግሎት ....38
12. የፕላንና ፕሮግራም አገልግሎት ....39
13. የአስተዳደርና ፋይናንስ አገልግሎት ....39
    13.1 የሰው ኃይል ሁኔታ ....39
    13.2 የበጀት አጠቃቀም ....41
    13.3 አገልግሎት ነክ የሆኑ ጉዳዮች ....45
14. በዕቅድ አፈጻጸም ሂደት ያጋጠሙ ችግሮች ....47

# የ1998 ዓ.ም የዘጠኝ ወራት
# የዕቅድ አፈፃፀም ግምገማ ሪፖርት

## 1. መግቢያ

የማዕከላዊ ስታቲስቲክስ ኤጀንሲ በየጊዜው አዳዲስ የመረጃ አሰባሰብ ስልቶችን በመቀየስ፣ በመንደፍና በመቅረጽ ማህበራዊ፣ ኢኮኖሚያዊና የስነ-ህዝብ መረጃዎችን በመሰብሰብ፣ በማቀነባበር፣ በመተንተንና በሪፖርት በማውጣት ለተጠቃሚዎች በማሰራጨት ላይ ይገኛል፡፡ እነዚህ መረጃዎች እንደተገልጋዩ ፍላጎት ለዕቅድም ሆነ ለምርምር እንደዚሁም ለሌሎች ሥራዎች መነሻ በመሆን ከፍተኛ አስተዋፅኦ እያበረከቱ ሲሆን፣

በ1998 በጀት ዓመትም መ/ቤቱ በብሔራዊ ስታቲስቲክስ ፕሮግራምና የአምስት ዓመቱን የስትራቴጂክ ዕቅድ መሠረት በማድረግ ለማከናወን ያቀዳቸውን የስታቲስቲክስ ጥናቶች ከላይ የተገለፀውን አጠቃላይ መርህ መሠረት በማድረግና የመ/ቤቱን የማስፈጸም አቅም እንዲሁም የተመደበለትን በጀት ግምት ውስጥ በማስገባት ለማከናወን አቅዶ በመንቀሳቀስ ላይ ነው፡፡

በዚህም መሰረት የመረጃ መሰብሰቡ ተግባር በ1997 ዓ.ም ተጀምሮ የመረጃ ማቀነባበሩ ተግባር ወደ 1998 የተሸጋገሩ የበልግ ወቅት የግብርና ናሙና ጥናት፣ የሰፋፊና መካከለኛ የግልና የመንግስት እርሻዎች ጥናት፣ የአትክልት፣ ሥራ ሥርና የቋሚ ሰብሎች ጥናት፣ የ1996 የትላልቅና መካከለኛ ማምረቻ ኢንድስትሪ ጥናት፣ የሰው ኃይል ጥናት እንዲሁም በውጭ ዕርዳታ የሚከናወኑ የኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ ደህንነት ጥናት፣ የቤተሰብ ገቢ ፍጆታና ወጪ ጥናት፣ የኤች.አይ.ቪ/ ኤድስ የባህሪ ቅኝት ጥናት ቀሪ ሥራዎችንና በርካታ አዳዲስ ጥናቶችን በማከናወን ላይ ይገኛል፡፡ እነዚህም ጥናቶች፣

ሀ. የተፈጥሮ ሃብትና የግብርና ስታቲስቲክስ

- የሰብል ምርት ትንበያ ጥናት
- የሰብል ምርት ጥናት በመኸር ወቅት
- የሰፋፊ የግል፣ የመንግሥትና የድርጅት እርሻዎች ጥናት
- የሰብል ምርት ጥናት በበልግ ወቅት
- የቤት እንስሳት፣ የዶሮ ኃብትና ንብ የያዙ ቀፎዎች ጥናት /በገጠር/

ለ. የኢንዱስትሪ ስታቲስቲክስ

- የትላልቅና መካከለኛ ማምረቻ ኢንዱስትሪዎች ጥናት /በከተማ/
- ወቅታዊ የማማረቻ የንግድና የአገልግሎት ሰጪ ድርጅቶች ጥናት /በከተማ/
- የማምረቻ ኢንዱስትሪዎች የምርት መጠንና የአምራቾች ዋጋ ጥናት በየሩብ ዓመት /በከተማ/
- የኮንስትራክሽን ጥናት
- የማዕድንና ቁፋሮ ጥናት
- የአነስተኛ ኢንዱስትሪዎች ጥናት
- የውጪ ንግድ ስታቲስቲክስ መረጃ ማሰባሰብና ማጠናቀር
- የትራንስፖርትና መገናኛ ስታቲስቲክስ መረጃ ማሰባሰብና ማጠናቀር፣

ሐ. የቤተሰብ በጀትና የዋጋዎች ስታቲስቲክስ

- የግብርና ምርቶች የአምራቾች ዋጋ ጥናት /በገጠር/
- የዕቃዎችና የአገልግሎቶች የችርቻሮ ዋጋ ጥናት /በከተማ/
- የሸማቾች ዋጋ መመዘኛ ኢንዴክሶች ዝግጅት /በዋናው መ/ቤት/
- የዓለም አቀፍ የንፅፅር ፕሮግራም

መ. የማኅበራዊ ስታቲስቲክስ

- ተከታታይ የሥራ ስምሪት ጥናት

ሠ. የቆጠራ ካርታ ሥራ ማካሄድ ናቸው፡፡

## 2. የኢኮኖሚ ስታቲስቲክስ

### 2.1 የተፈጥሮ ሃብትና የግብርና ስታቲስቲክስ

### 2.1.1 የሰብል ምርት ትንበያ ጥናትን በተመለከተ

- የ1998 ዓ.ም የሰብል ምርት ትንበያ ጥናት መረጃ የተሰበሰበባቸው መጠይቆች ዋናው መ/ቤት ደርሰው ለኤዲቲንግና ቬሪፊኬሽን ሠራተኞች ሥልጠና በመስጠት ቀደም ሲል የነበረውን አሰራር በማሻሻልና አዳዲስ አሰራሮች እንዲካተቱ በማድረግ የእርማትና የቬሪፊኬሽን ሥራ ተጠናቋል፡፡ በተንሄደው የቬሪፊኬሽን ስራ የታዩ ግድፈቶችን በመለየት ለዋናው መኽር ጥናት የሚሰበሰበውን የመረጃ ጥራት ከፍ ለማድረግና የእርምት እርምጃ ለመውሰድ የሚያስችል የአሰራር መመሪያ ለቅ/ጽ/ቤቶች እንዲላክ በማድረግ ቀጣይ ሥራዎች ከአሁኑ በበለጠ በጥራት የሚሠሩበት ሁኔታ ተመቻችቷል፡፡

- ለ1998 ዓ.ም የሰብል ምርት ትንበያ ጥናት ለቬሪፊኬሽን የሚያገለግል መመሪያና ኮድ ቡክም አሻሽሎ በማዘጋጀት ሥራ ላይ እንዲውል ተደርጓል፡፡

- ከመስክ የመረጃ ማሰባሰቡ ሥራ የተጠናቀቀለት የ1998 የሰብል ምርት ትንበያ ጥናት በሰብል የተሸፈነ መሬትና በሌላ የመሬት አጠቃቀም የተያዘ የመሬት ስፋት መረጃዎች በዞን፣ በክልልና በሀገር አቀፍ ደረጃ ተቀነባብሮና ተዘጋጅቶ ለየክልሉ የግብርናና የገጠር ልማት ቢሮዎችና የፋኦ የምግብ አቅርቦትና የሰብል ግምገማ ቡድን ለሚያካሄዱት የሰብል ምርት ግምገማ ሥራ በግብአትነት መጠቀም እንዲችሉ ተሰጥቷል፡፡

- ከመስክ የመረጃ ማሰባሰቡ ተግባር የተጠናቀቀለት የ1998 የሰብል ምርት ትንበያ ጥናት በኮምፒውተር በማቀነባበር ካለፉት ሁለት ዓመታት መረጃዎች ጋር በማነፃፀር ሪፖርቱ ተዘጋጅቶ ለተጠቃሚዎች እንዲሰራጭ ተደርጓል፡፡

- በማዕከላዊ ስታቲስቲክስ ኤጀንሲን በክልል የግብርና ቢሮዎች አማካኝነት በየዓመቱ የሚወጡት የሰብል ምርት ትንበያ መረጃዎች መካከል ከፍተኛ ልዩነት በመፈጠሩ በመረጃ ተጠቃሚዎች ላይ ችግር ፈጥሯል፡፡ ይህንን

ችግር ለመቅረፍና የተጣጣመ መረጃ ለተጠቃሚዎች ለማቅረብ በገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ሚኒስቴር መ/ቤት ሰብሳቢነት የየክልሉ የመስተዳድር፣ የግብርና ቢሮ ኃላፊዎች የማ.ስ.ኤ ኃላፊዎችና ባለሙያዎች ስብሰባዎችን በማካሄድ በተወሰነ ደረጃ መግባባት ላይ በመድረሱ፣ ችግሩን ለአንዴና ለመጨረሻ ጊዜ ዕልባት ለመስጠት ቀጣይ ውይይትና ግምገማ ለማድረግ የቴክኒካል ኮሚቴ ተቋቁሟል። የኤጀንሲው ባለሙያዎች በቴክኒክ ኮሚቴው ስብሰባ ላይ በመሳተፍና ተከታታይ ስብሰባ በማድረግ ውጤቱንና የውሳኔ ሃሳብ ለStreering ኮሚቴ ለማቅረብ ዝግጅት እየተደረገ ነው።

### 2.1.2 የእርሻ መሬት ስፋትና የምርት መጠን መረጃ በተመለከተ

- የ1997 ዓ.ም የበልግ ወቅት ጥናት መረጃ የኤዲቲንግ፣ ኮዲንግና የቬሪፊኬሽን ሥራ ተካሂዶ፤ የታረሰ መሬት ስፋትና ምርት መጠን የመረጃ ቅንብር፣ የትንተናና የሪፖርት ዝግጅቱ ሥራ ተከናውኖና ታትሞ ሪፖርቱ ለመረጃ ተጠቃሚዎች እንዲሠራጭ ተደርጓል። እንዲሁም ለ1998 በልግ ጥናት ተጨማሪ የማሻሻያ መጠይቅና መመሪያ ተዘጋጅቷል።

- የ1998 የመኸር ወቅት በሰብል የተያዘ መሬት ስፋትና ምርት መጠን የኤዲቲንግ ኮዲንግ፣ ቬሪፊኬሽንና የዳታ ኢንትሪ ሥራ የተጠናቀቀ ሲሆን፣ የዳታ ክሊኒንግ ሥራም በአብዛኛው ተጠናቋል።

### 2.1.3 የመሬት አጠቃቀም

- የ1997 ዓ.ም የመኸር ወቅት የመሬት አጠቃቀም /Land use/ ውጤት ስታቲስቲካል ሪፖርት ዝግጅት ተጠናቆና ታትሞ ለተጠቃሚዎች ተሠራጭቷል።

- የ1998 የመኸር ወቅት የመሬት አጠቃቀም መረጃ እስከ ዳታ ኢንትሪ ድረስ ያለው የተጠናቀቀ ሲሆን፣ የዳታ ክሊኒንግ ሥራ በመከናወን ላይ ይገኛል።

### 2.1.4 የእርሻ ሥራ አጠቃላይ ሁኔታን በተመለከተ

- የ1997 ዓ.ም የመኸር ወቅት የእርሻ ሥራ አጠቃላይ ሁኔታ ጥናት ውጤት የሆነው የስታቲስቲካል ሪፖርት ዝግጅትና ሕትመት ሥራ ተጠናቆ ለተጠቃሚዎች እንዲሰራጭ ተደርጓል፡፡

- ከመስክ የመረጃ መሰብሰቡ ተግባር የተጠናቀቀለት የ1997 የበልግ ወቅት የእርሻ ሥራ አጠቃላይ ሁኔታ ጥናት በኮምፒውተር የማቀነባበሩ ሥራ ተካሄዶ፤ የትንተናና የስታቲስቲካል ሪፖርት ዝግጅቱ ሥራ ተጠናቆና ታትሞ ለመረጃ ተጠቃሚዎች ተሰራጭቷል፡፡

- የ1998 የመኸር ወቅት የእርሻ ሥራ አጠቃላይ ሁኔታ መረጃ እስከ ዳታ ኢንትሪ ድረስ ያለው ሥራ ተጠናቆ፣ የዳታ ክሊኒንግ ሥራ በመካሄድ ላይ ይገኛል፡፡

### 2.1.5 የቤት እንስሳት የዶሮ ሃብትና ንብ የያዙ ቀፎዎችን በተመለከተ

- የ1998 ዓ.ም የቤት እንስሳት ዶሮ ሃብትና ንብ የያዙ ቀፎዎች ጥናትን በተመለከተ ለመረጃ መሰብሰብ ተግባር የሚያገለግሉ የኤዲቲንግና ኮዲንግ መመሪያ ተዘጋጅቶ፤ ለሚመለከታቸው ባለሙያዎች ስልጠና ተሰጥቷል፡፡

- በ1998 ዓ.ም የቤት እንስሳት ጥናት መረጃ ውጤት መስፈሪያ የሚያገለግል የ Tabulation Plan ተዘጋጅቶ ለሚመለከተው መምሪያ የተላለፈ ሲሆን፤ የሪፖርት ዝግጅቱም ተጠናቆ ለህትመት ተልኳል፡፡

### 2.1.6 የሰፋፊና የመካከለኛ ንግድ እርሻዎች መረጃን በተመለከተ

በ1997 ዓ.ም የመረጃ ማሰባሰቡ ተግባር የተጠናቀቀለት የሰፋፊና የመካከለኛ እርሻዎች ጥናት የኤዲቲንግ፣ ኮዲንግና ቬሪፊኬሽን የዳታ ኢንትሪና የመረጃ ቅንብሩ ሥራ ተጠናቆ፣ የሪፖርት ዝግጅቱ ሥራ በመካሄድ ላይ ይገኛል፡፡ እንዲሁም ለ1998 የሰፋፊና መካከለኛ እርሻዎች ጥናት የሚያገለግል መጠይቅና መመሪያ ተዘጋጅቶ ለህትመት ተልኳል፡፡

### 2.1.7 ሌሎች የተከናወኑ ተግባት

- ለ1998 ዓ.ም ለቅድመ ማስጠንቀቂያ፣ ለመኸር፣ ለበልግ ወቅትና ለቋሚ ሰብል ምርት ትንበያና ለግብርና ናሙና ጥናት ከመስክ መረጃ ለመሰብሰብ የሚያስችሉ አስፈላጊ የሆኑ ማሻሻያዎችንና አዳዲስ ቅጾችን ያካተቱ መጠይቆችና መመሪያዎች ተዘጋጅተው ሥራ ላይ ውለዋል፡፡

- ለ1998 ዓ.ም የቅድመ ማስጠንቀቂያ፣ የሰብል ምርት ትንበያ፣ ለዋናው መኸር ግብርና ናሙና ጥናት፣ ለቤት እንስሳት ጥናት ለበልግ ወቅት ጥናት ለሰፋፊና መካከለኛ እርሻዎችን ጥናት በሚመለከት ከነሐሴ አጋማሽ ጀምሮ ለ20 ቀናት በ25ቱም ቅ/ጽ/ቤቶች ለመረጃ ሰብሳቢዎችና ለመስክ ተቆጣጣሪዎች ስልጠና ተሰጥቷል፡፡

- በ1998 ዓ.ም ለሚካሄደው የምግብ ዋስትና ጥናት ማዘጋጃ የሚያገለግሉ Tabulation Plan ዝግጅት የተጠናቀቀ ሲሆን፣ በግብርና ቆጠራ መረጃ ላይ መሠረት ያደረገ ለኢትዮጵያ ግብርና አትላስ ዝግጅት የሚያገለግል የትርጉም ሥራ ተካሄዷል፡፡

- መ/ቤቱ በየዓመቱ ለሚያዘጋጀው የስታቲስቲክስ መጽሔት መምሪያውን የሚመለከት መረጃዎች ከሌሎች መ/ቤቶች፣ በማሰባሰብና በመምሪያው የሚገኙትንም የማጠናቀር ሥራ ተጠናቆ ለሚመለከታቸው ተላልፏል፡፡

- የ1997 ዓ.ም የቋሚ ሰብል፣ አትክልትና ሥራ ሥር ተክሎች ልዩ ጥናት መረጃ የኤዲቲንግ፣ ኮዲንግና ቬሪፊኬሽን ሥራ ተጠናቆ፤ መረጃውን ወደ ኮምፒውተር የማስገባትና በማጽዳት፤ ውጤቱ በመገምገም ላይ ይገኛል፡፡

- ከ10 የቆጠራ ቦታዎች ላይ ከሚሰበሰብ የታረሰ መሬት ስፋት መረጃ ግብዓትነት በሳተላይት ለሚደረገው ግምገማ መረጃዎች ከሦስት የቆጠራ ቦታዎች ተሰብስቦ የኤዲቲንግ፣ ኮዲንግና ቬሪፊኬሽን ሥራ ተጠናቆ፤ውጤቱን ከFAO ባለሙያዎች ጋር ለማነፃፀር ዝግጅቱ ተጠናቋል፡፡

- ለዋናው መኽር ጥናት ኤዲቲንግ ኮዲንግና ቬሪፌኬሽን የሚያገለግሉ መመሪዎች ኤዲት ስፔሲፊኬሽንና Tabulation Plan ዝግጅት ተጠናቆ ለሚመለከተው ተሰጥቷል፡፡

- ማ.ስ.ኤ ለመጀመሪያ ጊዜ ለሚያጠናው የ1998 የምግብ ዋስትና ጥናት የተጠናቀሩ መረጃዎችን ለተጠቃሚ ለማቅረብ የሚያስችሉ ንድፍ ሠንጠረዦች፣ (Tabulation Plan) የኤዲቲንግ ኮዲንግ መመሪያና የኮምፒውተር ኤዲት ስፔስፊኬሽን ዝግጅት ሥራ ተጠናቆ ለሚመለከተው ክፍል ተላልፏል፡፡

2.2 <u>የቤተሰብ በጀትና የዋጋዎች ስታቲስቲክስ</u>

2.2.1 <u>የዋጋዎች ጥናትና የዋጋ ኢንዴክስን በተመለከተ</u>

ሀ. <u>በገጠር የግብርና ውጤቶች የአምራቾች ዋጋ ጥናት</u>

- የአምራቾች ዋጋ ጥናት የመረጃ አሰባሰብ መመሪያ በማዘጋጀት ለመረጃ ሰብሳቢዎችና ለመስክ ተቆጣጣሪዎች ስልጠና የተሰጠ ሲሆን፣ ለዕቅድ ዓመቱ የሚያገለግል መጠይቅም ታትሞ ለቅ/ጽ/ቤቶች እንዲሠራጭ ተደርጓል፡፡

- ከሐምሌ ወር 1997 እስከ ታህሣሥ ወር 1998 ዓ.ም ያለው የአምራቾች ዋጋ ጥናት ተጠናቆና ታትሞ ለተጠቃሚዎች ተሠራጭቷል፡፡ እንዲሁም የጥርና የየካቲት ወር መረጃ ተዘጋጅቶ ለህትመት የተላከ ሲሆን፣ የመጋቢት ወር 1998 መረጃ በመቀነባበር ላይ ይገኛል፡፡

ለ. <u>ወርሃዊ የዕቃዎችና የአገልግሎቶች ዋጋ ጥናት</u>

- ለጥናቱ የመረጃ አሰባሰብ መመሪያን በማዘጋጀት ለመረጃ ሰብሳቢዎችና ተቆጣጣሪዎች ስልጠና በመስጠት የመረጃ መሰብሰብ ተግባር በመካሄድ ላይ ይገኛል፡፡ እንዲሁም ለዕቅድ ዓመቱ የሚያገለግል መጠይቅ ተባዝቶ ለቅ/ጽ/ቤቶች ተሰራጭቷል፡፡

- ከሐምሌ ወር 1997 ዓ.ም እስከ ጥር 1998 ዓ.ም ያለው ሪፖርቱ ተዘጋጅቶ ለተጠቃሚዎች ተሰራጭቷል። እንዲሁም የየካቲት ወር 1998 መረጃ ተቀነባብሮ ለህትመት የተላከ ሲሆን፣ የመጋቢት ወር 1998 መረጃ በመቀነባበር ላይ ይገኛል።

ሐ. ወርሃዊ የሸማቾች ዋጋ መመዘኛ ጠቋሚ አሃዝ

- የሃገር አቀፍና የክልሎች

  - የሀገር አቀፍና የክልሎች የሸማቾች ዋጋ መመዘኛ ጠቋሚ አሃዝ ከሐምሌ ወር 1997 ዓ.ም እስከ የካቲት 1998 ዓ.ም ድረስ ያለው መረጃ በየወሩ ታትሞ ለተጠቃሚዎች እንዲደርስ ተደርጓል።

  - የመጋቢት ወር 1998 ዓ.ም አሃዝ በመቀነባበር ላይ ይገኛል።

- የአዲስ አበባ ከተማ

  - የአዲስ አበባ ከተማ የሸማቾች ዋጋ መመዘኛ ጠቋሚ አሃዝ ከሐምሌ ወር 1997 ዓ.ም እስከ መጋቢት 1998 ዓ.ም ድረስ ያለው መረጃ በየወሩ እየተቀነባበረና እየታተመ ለተጠቃሚዎች በወቅቱ ተሰራጭቷል።

መ. የዓለም አቀፍ ንጽጽር መርሃ -ግብር በአፍሪካ

ይህ ጥናት የአፍሪካ ሃገሮችን ገንዘብ የመግዛት አቅም ለማስላት የሚያስችል ጥናት ሲሆን፤ ከአፍሪካ ልማት ባንክ እና ከምሥራቅና ደቡብ አፍሪካ የንግድ ቀጠና (COMESA) ጋር በመተባበር በመ/ቤቱ የሚካሄድ ነው። በመሆኑም በዚህ ዘጠኝ ወር ውስጥ የሚከተሉት ተግባራት ተከናውነዋል።

- የቅድመ ዝግጅት ሥራን በሚመለከት

  - ለጥናቱ የሚያስፈልጉ ዶኩመንቶችን የማሰባሰብ፣ የድርጅቶች መመዝገቢያ ቅጾችን፣ የመረጃ ማሰባሰቢያ መጠይቆችንና መመሪያዎችን የማሻሻልና

የእርምት ሥራ ተከናውኗል፡፡ የድርጅቶች መመዝገቢያ ቅጽ የመረጃ አሰባሰብ መመሪያና ለ12 ወራት መረጃዎችን ለማሰባሰብ የሚያስችል መጠይቆች እንዲባዙ ተደርጓል፡፡

- ለቅ/ጽ/ቤቶች የመስክ ሠራተኞችና ባለሙያዎች በዋናው መ/ቤት ከታህሳስ 10-17/1998 ዓ.ም ድረስ ሥልጠና ተሰጥቷል፡፡ ለጥናቱ አስፈላጊ የሆኑ ግብዓቶችን ለማግኘት ደብዳቤ የመጻፍ ሥራ በሀገር ውስጥ ለሚገኙ ተቋማትና በውጭ ለሚገኙ ለአፍሪካ ልማት ባንክና ከምሥራቅና ደቡብ አፍሪካ የንግድ ቀጠና (COMESA) ባለሙያዎች ጋር የተከናወነ ሲሆን፤ ለጥናቱ አስፈላጊ የሆኑ ቁሳቁሶች ግዥ በመካሄድ ላይ ይገኛል፡፡ ጥናቱን ለማስተዋወቅ የሚያችል ጽሁፍ በማዘጋጀት የመገናኛ ብዙሃንን በመጠቀም መግለጫ ተሰጥቷል፡፡

- <u>መረጃ የማሰባሰብና የማቀነባበር ተግባራትን በሚመለከት</u>

  - በአገር አቀፍ ደረጃ ለICP መረጃ መሰብሰብ የሚያስችሉ በደንበኝነት ለሚያዙ ድርጅቶች ምዝገባና መረጣ ከታህሳስ 20 -23/1998 ባለው ጊዜ ተካሄዷል፡፡

  - የዚህ ጥናት መረጃ የማሰባሰቡ ተግባር ከሐምሌ 1997 እስከ ታህሣስ 1998 ዓ.ም ድረስ በአዲስ አበባ እንዲሁም ከጥር 1998 እስከ መጋቢት 1998 ድረስ በሁሉም ክልሎች ተጠናቋል፡፡

  - የዚህ ጥናት መረጃ በኮምፒውተር የማረምና የማስተካከል ሥራ ምንም እንኳን በአገር አቀፍ ደረጃ የሚከናወን ቢሆንም መረጃ የማጥራቱ ሥራ የመጨረሻ የሚሆነው የተሰበሰበው መረጃ ከሌሎች የአፍሪካ አገሮች መረጃ ጋር ተወዳድሮ አጥጋቢ ሲሆን ብቻ ነው፡፡ በመሆኑም ከሐምሌ ወር 1997 እስከ ታህሳስ ወር 1998 ዓ.ም ድረስ ያለው መረጃ ከ (COMESA) አገሮች መረጃ እንዲሁም ከሁሉም አገሮች መረጃ ጋር ተወዳድሮ መጠነኛ አለመጣጣም ለታየባቸው መረጃዎች በድጋሚ ማስተካከያ ተደርጎ ወደ አፍሪካ ልማት ባንክ ተልኳል፡፡

- የየካቲት ወር 1998 የአዲስ አበባ ከተማ የዓለም አቀፍ ንጽጽር መርሃ ግብር መረጃ የዳታ ኤዲቲንግ ኮዲንግና ኢንትሪ ሥራ ተካሄዶ የመረጃ ማቀነባበሩ ሥራ በመካሄድ ላይ ይገኛል::

- በICP Africa ዋጋ ጥናት መረጃ ላይ በመረጃ እርማት ወቅት የታዩ ችግሮችን በመሰብሰብና ተጨማሪ መመሪያም በማዘጋጀት ከመስክ ሠራተኞች ጋር ውይይት በማድረግና ዶኩመንት በመስጠት ግድፈቶች በቀጣይ ሥራ ወቅት እንዳይደገሙ ለማድረግ ጥረት ተደርጓል::

- የዚህ ጥናት አካል የሆነው የመድሃኒት ዋጋ መረጃ የታህሳስና የየካቲት ወር ተሰባስቦና የእርማት ሥራ ተሠርቶ ለአፍሪካ ልማት ባንክ ተልኳል::

- የነዳጅ ዋጋ ንረት በኢኮኖሚ ያለው ተፅዕኖን በሚመለከት መረጃ የማሰባሰብ ተግባር ከህዳር 5 እስከ ታህሳስ 5 1998 ድረስ በአዲስ አበባ ከተማ ከሚገኙ ትላልቅ የነዳጅ ማደያ ድርጅቶች ተካሄዶ፣ መረጃው ኮምፒውተር ተቀነባብሮ ለአፍሪካ ልማት ባንክ ተልኳል::

- የገበያ መረጃ ስርዓትን በሚመለከት ከምግብ ዋስትና ማስተባበሪያ ቢሮ በቀረበ ጥያቄ መሠረት ለጥናቱ የሚሆን ፕሮጀክት በማዘጋጀትና በጀቱንም በማፅደቅ ለክልል የምግብ ዋስትና ማስተባበሪያ ቢሮዎች በመላክ በአማራ፣ በኦሮሚያ፣ በትግራይና በደቡብ ብሔር ብሔረሰቦች ክልሎች በተመረጡ 144 የመገበያያ ቦታዎች መረጃውን በየሳምንቱ የማሰባሰብ ተግባር በመካሄድ ላይ ይገኛል::

### 2.2.2 የቤተሰብ ገቢ, ፍጆታና ወጪ, ጥናትን በተመለከተ

- በቤተሰብ ገቢ, ፍጆታና ወጪ, ጥናት የቤተሰብ አባላት ከቤት ውጭ የተመገቧቸው ምግቦች መመዘን ባለመቻሉ በአዲስ አበባ ከተማ ከሚገኙ ምግብ ቤቶች ናሙና በመውሰድ በቁጥር የተመዘገበውን ከቤተሰብ ገቢ, ፍጆታና ወጪ, ጥናት ከተገኘው መረጃ ጋር በማቀናጀት ወደግራም ለመቀየር የሚያስችሉ አማካይ ማባዣዎች ተዘጋጅተው ጥቅም ላይ ውለዋል:: እንዲሁም ከቤት ውጭ የተወሰዱ የምግብና የመጠጥ መረጃዎች ወደ ካሎሪ ለመቀየር የሚያስችል የአሠራር ዘዴ

ተቀይሶ ጥቅም ላይ የዋለ ሲሆን፣ ሪፖርቱ የሚወጣበት የሠንጠረዥ ዝግጅቶች ተጠናቀው ለሚመለከተው አካል ተላልፏል፡፡

- የጥናቱን መረጃ ይበልጥ ለማጥራት ሲባል የተሻሻሉ መመሪያዎችን በማዘጋጀት በሥራው ላይ ለሚሳተፉ ባለሙያዎች ሥልጠና በመስጠት ወደ ሥራው እንዲሠማሩ ተደርጓል፡፡ ከጥናቱ ጐን ለጐን የተጠናው የዕቃዎችና አገልግሎቶች የችርቻሮ ዋጋ መረጃ የማጥራት ሥራ የተካሄደ ሲሆን የመረጃ ጥራትን በኮምፒውተር ለመቆጣጠርና ለማረም የሚያስችል መመሪያ ኤዲት ስፔስፊኬሽን ተዘጋጅቷል፡፡

- ተአማኒነት የሚጐድላቸውን መረጃዎች ለመቆጣጠር እንዲቻል በቤተሰብ ገቢ ፍጆታና ወጪ አማካኝነት የተሰላውን አማካይ ዋጋ ጥናት የተገኘውን አማካይ ዋጋ በቤተሰብ ደረጃና በያንዳንዱ ዕቃ ደረጃ እንዲነጻጸር ተደርጓል፡፡

- ከቤተሰብ ገቢ፣ ፍጆታና ወጪ ጥናት የተሰበሰቡ የመጠንና የዋጋ መረጃዎች መጣጣማቸውንና መቃረናቸውን ለመቆጣጠር ሲያገለግል የነበረው የአገር አቀፍ የዋጋ መረጃ ጠቀሜታው የጎላ ባለመሆኑ ለእያንዳንዱ ክልል የራሱ የዋጋ ጥናት መረጃ ለመጠቀም እንዲቻል የዋጋ መረጃዎቹን የጥራት ደረጃ የሚያስጠብቅ ሥራ ተካሄዷል፡፡

### 2.2.3 <u>የኢኮኖሚና ማህበራዊ ደህንነት ጥናት በተመለከተ</u>

በ1996 በጀት ዓመት የመረጃ መሰብሰብ ተግባር የተጠናቀቀለት የኢኮኖሚና ማህበራዊ ደህንነት ጥናት የመረጃ ማቀነባበርና የሪፖርት ዝግጅቱ ተጠናቆና ታትሞ ለመረጃ ተጠቃሚዎች ተሰራጭቷል፡፡

### 2.2.4 <u>ልዩ ልዩ ሥራዎች</u>

- በእንግሊዘኛ ተዘጋጅቶ የነበረውን በ 5 ዓመቱ የልማት ዕቅድ ውስጥ ለተንተተው የክትትል የግምገማ ስርዓት ሰነድ ወደ አማርኛ እንዲተረጐም ተደርጓል፡፡

- መ/ቤቱ ለሚያዘጋጀው ዓመታዊ ስታቲስቲክስ መጽሔት የሚያገለግሉ ዘርፉን የሚመለከቱ መረጃዎች ከልዩ ልዩ መ/ቤቶች ተሰባስበውና ተቀነባብረው ለሚመለከተው አካል ተሰጥተዋል።

2.3 <u>የኢንዱስትሪ፣ ንግድ ትራንስፖርት መገናኛ ስታቲስቲክስ</u>

2.3.1 <u>የኢንዱስትሪ ስታቲስቲክስ ጥናቶች በተመለከተ</u>

ሀ. <u>የትላልቅና መካከለኛ ማምረቻ ኢንዱስትሪዎች ጥናት</u>

- በ1997 የዕቅድ ዘመን የመረጃ ማሰባሰቡ ተግባር የተጠናቀቀለት የ1996 በጀት ዓመትን የሚመለከተው የትላልቅና መካከለኛ ማምረቻ ኢንዱስትሪዎች ጥናት ሙሉ በሙሉ ተጠናቆ ሪፖርቱ ለተጠቃሚዎች ተሰራጭቷል።

- ከጃንዋሪ 2005 እስከ ዲሴምበር 2005 ድረስ ያለው የManufacturing የአምራቾች ዋጋ ተሰብስቦ፣ ተጠናቅሮ፣ ኢንዴክሱ ተሰልቶና ተተንትኖ መረጃ ተጠቃሚዎች አስተያየት እንዲሰጡበት ለሚመለከታቸው መ/ቤቶች ተልኳል።

- የ1997 የአራተኛ ሩብ ዓመት የማምረቻ ኢንዱስትሪዎች ወቅታዊ ጥናትና የ1998 የመጀመሪያና የሁለተኛ ሩብ ዓመት ጥናት ከመረጃ መሰብሰብ እስከ ሪፖርት ዝግጅት ድረስ ያለው ሥራ ተከናውኖ ሪፖርቱ ለተጠቃሚዎች ተሰራጭቷል።

- በ1998 ዓ.ም የመረጃ መሰብሰቡ ተግባር ለሚካሄድለት የ1997 ዓ.ም የትላልቅና መካከለኛ ኢንዱስትሪዎች ጥናት የመጠይቅና መመሪያ ዝግጅት ተጠናቆ ለመረጃ ሰብሳቢዎች፣ ተቆጣጣሪዎችና ስታቲስቲሺያኖች ስልጠና ተሰጥቷል።

ለ. <u>የአነስተኛ ማምረቻ ኢንዱስትሪዎች ጥናት</u>

ለአነስተኛ ማምረቻ ኢንዱስትሪዎች ጥናት የመጠይቅና የማንዋሎች ዝግጅት ሥራ ተከናውኖ ለመረጃ ሰብሳቢዎችና ለተቆጣጣሪዎች እንዲሁም

ለስታቲስቲሽያኖች ሥልጠና ተሰጥቶና የመረጃ ማሰባሰቡ ተግባር ተጠናቆ በቢሮ ደረጃ የኤዲቲንግ ሥራውን ለመጀመር ዝግጅት እየተደረገ ነው።

ሐ. <u>የኢኮኖሚ ድርጅቶች ቆጠራ</u>

በ1995 ዓ.ም ጥናቱ ለተካሄደለት የኢኮኖሚ ድርጅቶች ቆጠራ መረጃን ጥራት ለማሻሻልና ዳታ ቤዝ ለመፍጠር ከዓለም ባንክ ከተላኩ አማካሪ ጋር በመሆን በርካታ ሥራዎች ተከናውኗል።

መ. <u>የንግድ ትራንስፖርት መገናኛና መጽሔት ፋይናንስ ስታቲስቲክስ</u>

- ለትራንስፖርትና መገናኛ መጽሔት የሚሆኑ መረጃዎች ከየመ/ቤቶች የመሰብሰብ ሥራ ተጠናቆ የመጽሔት ዝግጅቱ ሥራ በመካሄድ ላይ ይገኛል።
- የዓመታዊ ስታቲስቲክስ መጽሔት ዝግጅት የሚሆኑ ሥራ የትራንስፖርትና መገናኛ መረጃዎች የመሰብሰብ ተግባር ተከናውኖ ለሚመለከተው ተላልፏል።
- ለአከፋፋይ ንግድ ጥናት የሚሆን የመጠይቅ ዝግጅት ሥራ፣ እንዲሁም የሙከራ ጥናት በሦስት ከተሞች ማለትም በአዲስ አበባ፣ ፍቼና ደብረብርሃን ተከናውኗል።
- የኢንፎርሜሽንና ኮሚኒኬሽን ቴክኖሎጂ አመልካች ላይ ጥናት ለማካሄድ የቅድመ ዝግጅት ሥራ በመከናወን ላይ ይገኛል።
- የውጭ ንግድ መረጃ ለጠየቁ መረጃ ተጠቃሚዎች አስፈላጊው መረጃ ተሰጥቷል።

ሠ. <u>የኮንስትራክሽን ጥናት</u>

በበጀት ዓመቱ ለሚካሄደው የኮንስትራክሽን ጥናት የመጠይቅ፣ የመመሪያና የፍሬም ዝግጅት ተጠናቆ፣ በመረጃ መሰብሰቡ ተግባር ላይ ለሚሣተፉ ባለሙያዎች አስፈላጊው ስልጠና ተሰጥቷል።

ረ. ሌሎች የተከናወኑ ሥራዎች

በዚህ ዓመት ለሚካሄዱ ጥናቶች በፍሬምነት የሚያገለግሉ የማምረቻ ኢንዱስትሪዎች፣ የግንባታ ሥራ ተቋራጮች፣ በድንጋይ አሸዋና ሌሎች ማዕድናትን በማምረት ሥራ ላይ የተሰማሩ ድርጅቶች ዝርዝር የማውጣት ሥራ ተከናውኗል።

## 3. የሥነ-ሕዝብና የማኅበዊ ስታቲስቲክስን በተመለከተ

### 3.1 የማህበራዊ ስታቲስቲክስን በተመለከተ

#### 3.1.1 የሰው ኃይል ስታቲስቲክስ

በ1997 ዓ.ም የመረጃ ማሰባሰቡ ተግባር የተጠናቀቀለት የሰው ኃይል ጥናትን በሚመለከት ለኤዲቲንግና ኮዲንግ መምሪያ ተዘጋጅቶ ሥልጠና ተሰጥቷል። የተሰበሰበው መረጃ የኤዲቲንግ፣ ኮዲንግና የማጥራት ሥራ ተጠናቆ ለህትመት የሚሆኑ ሠንጠረዦች ተመርጠው በመዘጋጀት ላይ ይገኛሉ።

#### 3.1.2 ተከታታይ የሥራ ስምሪት ጥናትን በተመለከተ

- በ1998 ዓ.ም ለሚካሄደው ተከታታይ የሥራ ስምሪት ጥናት ደጋፊ የሚሆኑ ዶክመንቶች የማሰባሰቡ ተግባር የተከናወነ ሲሆን፣ የሥራ መርሃ ግብር፣ የመረጃ ማሰባሰቢያ መጠይቆች፣ የመረጃ ሰብሳቢና የተቆጣጣሪዎች መመሪያዎችና የድርጅት ዋና ምርት/አገልግሎት ምደባና መለያ ኮደ መጽሐፍ ተዘጋጅተው ሥራ ላይ ውለዋል።

- የመስክ ሥራ አፈጻጸም መመሪያ ተዘጋጅቶ ለሚመለከተው ክፍል የተላላፈ ሲሆን፤ በተዘጋጁት መጠይቆች ላይ ከሚመለከታቸው መ/ቤቶች አስተያየት ተሰብስቦ፤ በመረጃ መሰብሰቡ ተግባር ላይ ለሚሰማሩ ባለሙያዎችና የመስክ ሠራተኞች አስፈላጊው ስልጠና ተሰጥቷል።

#### 3.1.3 የትምህርት ባህልና ስፖርት ስታቲስቲክስን በተመለከተ

- ለ1997 ዓ.ም ዓመታዊ ስታቲስቲክስ መጽሔት ዝግጅት የሚያስፈልጉ የትምህርት፣ የባህልና ስፖርት፣ የጤና፣ መረጃዎችን ለመሰብሰብ የሚያስችሉ መጠይቆችና ቅጾች ለሚመለከታቸው የክልልና የፌዴራል

መ/ቤቶች ተልከው መረጃዎች ተሞልተው የተመለሱ ሲሆን፣ ለተጠቃሚዎች በሚያመች ሁኔታ ተጠናቅረው ለሚመለከተው ክፍል ተላልፊዋል::

- በ1996 ዓ.ም ከክልል ተሞልተው የመጡ የትምህርት መጠይቆች ተፈትሸው የታዩ ጉድለቶች እንዲስተካከሉ ለማድረግ አንድ ጥራዝ ተዘጋጅቶ ለሚመለከታቸው የስታቲስቲክስ ቅ/ጽ/ቤቶች ተልኳል::

- ለዓመታዊ መጽሔት ዝግጅት መረጃዎች ከክልልና ከፌዴራል መ/ቤቶች ተሞልተው ሲመጡ ወደ ኮምፒውተር የሚገቡበትና የሚጠናቀሩበት እንዲሁም መጽሔት ታትሞ ሲወጣ ተጠቃሚዎችን የሚያረካ እንዲሆን የሚያስችል ሠንጠረዥ ተዘጋጅቷል::

### 3.1.4 የሕግና ደንብ ስታቲስቲክስ በተመለከተ

- ለ1997 ዓመታዊ መጽሔት ዝግጅት የመረጃ ማሰባሰቢያ ቅጾች ለስታቲስቲክስ ቅ/ጽ/ቤቶችና በአዲስ አበባ ውስጥ ለሚገኙ ለሚመለከታቸው ለፌዴራልና ለክልል ቢሮዎች ተልከው መረጃዎች ተሞልተው ከመጡ በኋላ ወደ ኮምፒውተር በማስገባትና በማቀነባበር ለሚመለከተው እንዲደርስ ተደርጓል::

- ህግና ደንብን በሚመለከተ የአሠራር ሥርዓትን በማሻሻል የሥራ መርሃ ግብር ተዘጋጅቷል::

- ከሁለተኛ ምንጭ የሚገኙ መረጃዎችን ይዘት ለማሻሻል ከመረጃ ሰጭ መ/ቤቶች ጋር ግንኙነት በመፍጠር ሊገኙ የሚችሉ መረጃዎችን ለማጥናት የሚያስችል ቅድመ ዝግጅት ተጠናቋል::

- ለ1999 ዓ.ም በኢትዮጵያ ለሚካሄደው የህዝብና ቤቶች ቆጠራ የአካል ጉዳተኞችን መረጃ ለመሰብሰብ የሚያስችል መጠይቅ ለማዘጋጀት መካተት የሚገባቸውን ጉዳዮች ከተለያዩ ዶኩመንቶች በማየትና የሌሎች አገሮችን ልምድ ግምት ውስጥ በማስገባት መካተት አለባቸው ተብሎ የታመነባቸውን መጠይቆች በማካተት ለማዘጋጀት የተሞከረ ሲሆን፣ ለዚሁ ተግባር የሚውል የቆጣሪዎች መመሪያም ተዘጋጅቷል:: እንዲሁም የወንጀልና የደህንነት

ጥናትን በሚመለከት አጭር መጠይቅና የቆጣሪዎች መመሪያ እንዲዘጋጅ ተደርጓል።

### 3.1.5 <u>የጤናና አመጋገብ</u>

- ቀደም ሲል የተዘጋጀውን የኤች. አይ. ቪ /ኤድስ የባህርይ ቅኝት ጥናት የኤዲቲንግና የኮዲንግ ማንዋል ግምገማ ተካሂዶ ለኤዲቲንግና ኮዲንግ ሠራተኞች ሥልጠና ተሰጥቷል።

- በባህርይ ቅኝት ጥናቱ በተካተቱ በአዲስ አበባ በሚገኙ 25 ት/ቤቶች ውስጥ የወንድና የሴት ተማሪዎች፣ የመምህራን፣ የቤተሰብ፣ የከባድ መኪናና የአገር አቋራጭ አውቶብስ ሾፌሮች፣ ከአርብቶ አደር፣ ከሴተኛ አዳሪ ሴቶችና፣ ከፖሊስ ሠራዊትና ከመከላከያ አባላት እንዲሁም ከፋብሪካ ሠራተኞች የተሰበሰበው መረጃ የኤዲቲንግና የቬሪፊኬሽንና የዳታ ኢንትሪ ሥራ ተጠናቋል። ከላይ ከተዘረዘሩት የህብረተሰብ ክፍሎች ጥናት መካከል የሴትና የወንድ ተማሪዎች የጥናት ውጤትን በሚመለከት የኤዲት፣ ስፔስፊኬሽን የክሊኒንግና ሪፖርት ሠንጠረዦች የተጠናቀቁ ሲሆን የሌሎች ጥናቶች ከታቡሌሽን ፕላን እስከ ዳታ ክሊኒንግ ድረስ ያለው ተጠናቋል።

- የባህርይ ቅኝት ጥናትን በተመለከተ መረጃዎች ሊጠናቀሩበት የሚችሉ የሠንጠረዥ ዝግጅትና ከሚመለከታቸው ተቋማት /ከወረዳዎች ወይም ከጤና ተቋማት ተጨማሪ መረጃዎችን ለማሰባሰብ የሚያስፈልጉ የመሠረታዊ መረጃዎችን አይነት የመለየት ሥራ ተጠናቋል።

- በአዲስ አበባ ከተማ ሲኒማና ትያትር ቤቶች መረጃ ለመሰብሰብ የሚያስችል መጠይቅና የአሞላል መመሪያ ተዘጋጅቶ ለየድርጅቶቹ የተላከ ሲሆን፣ የመ/ቤቱ ባለሙያዎች በየድርጅቶቹ በመዘዋወር መረጃ በትክክል እንዲሞላ በማድረግ ሙያዊ እገዛ እያደረጉ ይገኛሉ።

- በጥናቱ በተካተቱ በ12 የተለያዩ የህብረተሰብ ክፍሎች መጠይቅ የኦዲቲንግና ኮዲንግ ሥራ ወደ ኮምፒውተር የማስገባት ሥራ ተከናውኗል።

- በየዓመቱ ለሚዘጋጀው ስታቲስቲክስ መጽሔት የሥነ ሕዝብና የጤና መረጃዎች ተዘጋጅተው ለሚመለከተው ተሰጥተዋል።

- በዓለም ጤና ድርጅት በHealth Net Work Matrix አማካይነት ለመ/ቤቱ የሚሰጠውን የሥራ ዝርዝሮችና የገንዘብ መጠን የዕርዳታ ዓይነት ለመለየት እንዲቻል ከጤና ጥበቃ ሚኒስቴር ባለሙያዎች ጋር በመተባበር ፕሮፖዛል ተዘጋጅቶ ተልኳል።

### 3.1.6 ሌሎች ሥራዎች

- ቀደም ሲል በተዘጋጀው የሥራ ውጤት ማሻሻያ (Business Process Enginering) ዶኩመንት ላይ አስተያየት ተዘጋጅቶ ለሚመለከተው ቀርቧል።

- ለተለያዩ መንግሥታዊና መንግስታዊ ላልሆኑ ድርጅቶች የመረጃ መስጠትና ሙያዊ ዕገዛ የማድረግ ተግበር ተከናውኗል።

- በህዝብና ቤቶች ቆጠራ የሚካተቱ የሰው ሃይል ጥናት መጠይቆችና የመጠይቅ አሞላል መመሪያዎች ዝግጅት ላይ የመምሪያው ባለሙያዎች ተሳትፈዋል።

## 3.2 የሕዝብና ቤት ቆጠራ የቅድመ ቆጠራ ዝግጅት ሥራዎችን በተመለከተ

### 3.2.1 የቆጠራ ቦታ ካርታ ሥራ

- በአገራችን ለሦስተኛ ጊዜ በ1999 ዓ.ም ለሚካሄደው የሕዝብና ቤት ቆጠራ አመቺ ሁኔታን ለመፍጠር እንዲቻል አገሪቱን በቆጠራ ቦታዎች የመሸንሸኑ ሥራ በበጀት ዓመቱ ዘጠኝ ወራት ውስጥ ተጠናክሮ የተካሄደ ሲሆን፣ በዕቅድ ዘመኑ ዘጠነኛ ወራት ውስጥ ድረስ የ21,932 የቆጠራ ቦታ ካርታዎች ተሰርተዋል።

- ለቆጠራ ቦታ ካርታ ሥራ የሚያስፈልጉ የመነሻ ካርታዎች፣ የተለያዩ ቅጾችና የጽሕፈት መሣሪያዎችን በማደራጀት ወደ ቅርንጫፍ ጽ/ቤቶች እንዲላኩ ተደርጓል። እንዲሁም ከየቦታው ለሚነሱ የቴክኒክ ጥያቄዎች ተገቢው ምላሽ

የተሰጠ ሲሆን በየቦታው የተጠናቀቁ የቆጠራ ቦታ ካርታዎችና ዶኩመንቶች ርክክብ ተደርጓል፡፡

- ለቆጠራ ቦታ ካርታ የመስክ ሥራ ላይ የተመደቡ ተሸከርካሪዎች ጋራዥ ገብተው በወቅቱ ተጠግነው እንዲወጡና ወደ መስክ እንዲሠማሩ አስፈላጊው ክትትል ተደርጓል፡፡

- የቆጠራ ቦታ ካርታ ሥራው በተሰጠው መመሪያ መሠረት እየተከናወነ መሆኑን ለመቆጣጠርና ለመገምገም እንዲሁም በሠራተኞች መካከል ጥሩ የሥራ ዲስፐሊን መኖሩን ለማረጋገጥ በማስተባበሪያው ያሉ ከፍተኛ ባለሙያዎች በኩል ተደጋጋሚ የመስክ ጉብኝት ተደርጓል፡፡

- የቆጠራ ካርታ ዲጂታይዜሽን ሥራ ለማፋጠን እንዲቻል የካርታ ሥራ ኤጀንሲ ባለሙያዎች አግባብነት ካለው የሥራ ዘርፍ የኤጀንሲውን ሠራተኞች በመመልመልና በማስተባበር በዲጂታይዜሽን ካርታ ሥራ ስልጠና እንዲያገኙ ተደርጓል፡፡

- ከመስክ ተጠናቀው የተላኩ የቤተሰብ ምዝገባና የኮርዲኔቶች ዝርዝር በተዘጋጀው የዳታ ኢንትሪ ፕሮግራም መሠረት በኮምፒውተር የመቅረጽ ተግባርና በጂ.አይ.ሴስ በመታገዝ የቆጠራውን ውጤት ለተጠቃሚ ለማቅረብ የ8 ወረዳዎች ካርታ የቀጣይነት ዲጂታይዝድ ተደርገዋል፡፡

- የገጠርና የከተማ የቤተሰብ መመዝገቢያ ቅጾች፣ የድንበርና የውስጥ ገጽታዎች መመዝገቢያ ቅጽ እንዲሁም መረጃዎችን ኤዲትና ኮድ በማድረግ የ10 ወረዳዎች በኮምፒውተር የመቅረጽ ሥራዎችና ሌሎች ተዛማጅ ሥራዎች ተከናውነዋል፡፡

- የትምህርት ሁኔታን በተመለከተ ካለፈው ቆጠራ ወዲህ በሥራ ላይ የዋለውን አዲሱን የትምህርት ፖሊሲ የትምህርት ደረጃዎች አከፋፈልና ዕውቅና የተሰጣቸው የግል ኮሌጆች ዝርዝር ከትምህርት ሚኒስቴር የተገኘ ሲሆን ቤቶችን በተመለከተ ደግሞ ከአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ባለሥልጣንና ከኪራይ ቤቶች አስተዳደር በተገኘው መረጃ መሠረት ጥያቄዎችና የመልስ አማራጮች ዝርዝር የመጀመሪያ ደረጃ ረቂቅ ተዘጋጅቷል፡፡

- የሕዝብና ቤት ቆጠራ ኮሚሽን እንደገና ለማቋቋም፣ በወጣው አዋጅ አንቀጽ 7 ተራ ቁጥር 5 መሠረት ኮሚሽኑ የተጣለበትን ኃላፊነት ለመወጣትና የብሔረሰቦች ብዛትና ሥርጭትን ለማወቅ የሚያስችል በቆጠራ ወቅት የሚሰበሰበውን የብሔረሰቦች ዝርዝር ለማዘጋጀት እንዲቻል ከፌዴሬሽን ምክር ቤት ጋር በመተባበር ሥራውን እየተካሄደ ያለ ሲሆን፣ እስካሁን ድረስ ከ3 ክልሎች ማለትም ከትግራይ፣ ከአፋርና አማራ በስተቀር የሌሎች ክልሎች ዝርዝር ደርሷል፡፡

### 3.2.2 ሌሎች የሕዝብና ቤት ቆጠራ የቅድመ ዝግጅት ሥራዎች በተመለከተ

- በ1999 ዓ.ም ለሚካሄደው የሕዝብና ቤት ቆጠራ የአካል ጉዳተኞችን መረጃ ለመሰብሰብ መካተት የሚገባቸውን ጥያቄ የማካተትና ዶክመንቶቹን የመለየት እንዲሁም የሌሎች አገሮች ልምድን ግምት ውስጥ በማስገባት የመረጃ ማሰባሰቢያ ቅጾችን ለማዘጋጀት ተሞክሯል፡፡

- የቆጠራውን የመጠይቅ አሞላል መመሪያ ዝግጅት፣ የጥያቄዎችንና መልሶችን ብዛትና ዓይነት ለመወሰንና ለማዘጋጀት በቆጠራው የሚሰበሰበውን የመረጃ ፍላጐት መወሰን እንዲቻል ከዋና ዋና መረጃ ተጠቃሚዎች አስተያየት የማሰባሰብ ሥራንና የሌሎች አገሮች ተሞክሮ በመፈተሽ የጥያቄዎች ዝርዝር ተዘጋጅቶ ለመ/ቤቱ የቆጠራ አስፈጻሚ ኮሚቴ በማቅረብ እንዲጸድቅ ተደርጓል፡፡

- የቆጠራው የእንግሊዝኛ፣ የአማርኛ፣ የገጠርና የከተማ አጭርና ረዥም መጠይቆች ዝግጅት ሥራ በአብዛኛው ተጠናቆ ለሚመለከታቸው የመ/ቤቱ ባለሙያዎች ለአስተያየት ተሰጥቷል፡፡

- የቆጠራውን መረጃ በአጭር ጊዜ ውስጥ ለተጠቃሚዎች ለማሠራጨት የእስካኒንግ ቴክኖሎጂ ጠቀሜታ ያለው መሆኑ ስለታመነበት ይህንን ቴክኖሎጂ ለ1999 የህዝብና ቤቶች ቆጠራ ዝግጅት ለመጠቀም እንዲቻል ከወዲሁ ሁኔታዎችን ለማመቻቸት ስለ አጠቃቀሙ ልምድ ለመቅሰም የመ/ቤቱ የሥራ ኃላፊዎችና ባለሙያዎች ወደ ታንዛኒያና ጋና በመሄድ የልምድ ልውውጥ አድርገው ተመልሰዋል፡፡

- በ1999 ለሚካሄደው ቆጠራ የገንዘብና የሎጂስቲክ ድጋፍ ለማስገኘት ቀደም ሲል የተዘጋጀውን Strategy and Implementation Plan for Census 2007 የሚለውን ሰነድ በመከለስ ከተባበሩት መንግሥታት ከስነ-ሕዝብ ጉዳይ ፈንድ ጋር በመተባበር ለጋሽ ድርጅቶችን በማነጋገር ለቆጠራው መሳካት ድጋፍ እንዲያደርጉ የመቀስቀስ ሥራ ከመሠራቱም ባሻገር የለጋሽ ድርጅቶች ስብሰባ እንዲደረግ የማስተባበር ሥራ ተካሄዷል፡፡

3.2.3 <u>ሁለተኛው ዙር የሥነ-ሕዝብና ጤና ጥናትን /DHS./ በተመለከተ</u>

የዓለም አቀፍ የናሙና ጥናት ፕሮግራም አካል የሆነውን የሥነ-ሕዝብና ጤና ጥናት ባለፈው የበጀት ዓመት በአገሪቱ ለሁለተኛ ጊዜ ለማካሄድ በዕቅድ ተይዞ የመስክ ሥራው ከመጋቢት ወር 1997 አጋማሽ ጀምሮ እስከ ነሐሴ 30 ቀን 1997 ሲካሄድ ቆይቷል፡፡ በዚሁ መሠረት በሥነ-ሕዝብ ማስተባበሪያ ሥር የሚገኙ መምሪያዎች በ1998 በጀት አመት በዘጠኝ ወራት ውስጥ የሚከተሉትን ዋና ዋና ተግባራት አከናውኗል፡፡

- በተለያዩ መምሪያዎች ሥር የሚገኙ ባለሙያዎች በተለያዩ ክልሎች መስክ በመውጣት የሥነ-ሕዝብና ጤና ጥናት የሥራ ሂደት የቴክኒክና የአስተዳደር ሥራዎች ማለትም የተሞሉ መጠይቆችን ኤዲት በማድረግና የመረጃ አሞላል ሂደቶችን በመመርመር፣ የተሽከርካሪዎች አቅርቦትና ሥርጭት፣ የደመወዝና የውሎ አበል አከፋፈል፣ በእያንዳንዱ ቡድን ውስጥ ያሉ መረጃ ሰብሳቢዎች የሥራ ድርሻቸውን አውቀው በጥሩ የሥራ ዲስፕሊን የተጣለባቸውን ኃላፊነት እየተወጡ መሆናቸውን በመገምገም ሪፖርት ቀርቧል፡፡

- ከመስክ ለሚነሱ የቴክኒክ ጥያቄዎችና አስተዳደራዊ ጉዳዮች /የተሽከርካሪ ብልሽት፣ የትብብር ማነስ፣ በሠራተኞች መካከል ለሚነሱ አለመግባባቶች... ወዘተ/ አፋጣኝ መፍትሔ መፈለግና የመስክ ሥራው ከተጠናቀቀ በኋላም የተሞሉ መረጃዎችና የመስክ ቁሳቁሶች ርክክብና ሌሎች ተያያዥ አስተዳደራዊ ሥራዎች ክንውንን ለመከታተል ተችሏል፡፡

- ከመስክ የተሞሉ ቅጾችንና መጠይቆችን ሁለት ዙር ኤዲትና ኮድ በማድረግ መረጃውን ወደ ኮምፒውተር ማስገባት፣ የመረጃ እርማት እና

የመረጃ የማቀነባበር /Data Processing/ ሥራዎች በተያዘላቸው ጊዜ ተጠናቀው የመጀመሪያ ደረጃ ሪፖርት በማዘጋጀት ለተጠቃሚዎች ተሠራጭቷል::

- ከዐብይ ኮሚቴ (Steering Committee) ና የቴክኒክ ኮሚቴ አባላት ጋር በየጊዜው ግንኙነት በማድረግ በሥራ ላይ ያጋጠሙ ችግሮችን ለመፍታት ስብሰባዎችን ማዘጋጀት ተችሏል:: እንዲሁም ለጥናቱ ቴክኒካዊ እገዛ ከሚያደርገው (ORC – MACRO) በየወቅቱ /በስልክ፣ በኢሜል፣ በአካል...ወዘተ/ በመገኘት የጥናቱ ቀሪ ሥራዎች በተያዘላቸው ፕሮግራም መሠረት ስለሚጠናቀቁበት መንገድ አስፈላጊውን መረጃ ለማቅረብ ተሞክሯል::

- ከመስክ የሚሰበሰበውን የደም ናሙና ከአስተባባሪዎች በጥንቃቄ በመረከብ ምርመራው ወደሚካሄድበት የኢትዮጵያ የሥነ ምግብ ጥናትና ምርምር ኢንስቲትዩት በወቅቱ ማስረከብ ተችሏል::

- በጥናቱ የመጀመሪያ ደረጃ ሪፖርት ላይ የተሰጡ አስተያየቶችን በማካተት የዋናው ሪፖርት ሥራ የተጀመረ ሲሆን፤ ለሪፖርቱ የተዘጋጁት ሠንጠረዦች ተገምግመው በአሁኑ ወቅት አብዛኛው የሪፖርቱ ምዕራፎች የመጀመሪያ ደረጃ ረቂቅ በመገባደድ ላይ ይገኛል:: በሪፖርት ዝግጅቱ የሚሳተፉ መ/ቤቶች ባለሙያ እንዲወክሉ በተጠየቀው መሠረት የአፈጻጸም ክትትል ተደርጐ በአሁኑ ወቅት በርዕስ በመከፋፈል ሪፖርቱ በመዘጋጀት ላይ ይገኛል::

- በጥናቱ ከተሰበሰቡት መረጃዎች መካከል አንዱ የኤች አይ ቪ መረጃ በመሆኑ ከዋና መረጃ ተጠቃሚዎች ጋር በተያዘው ፕሮግራም መሠረት ከMACRO ጋር በመሆን የ2 ቀን ስብሰባ ተካሄዷል:: በስብሰባው ወቅት በተነሱ ቴክኒካዊ ጥያቄዎች መሠረት በተከታታይ ለ3 ሳምንታት በተለያየ ደረጃ ስብሰባዎችና ውይይቶች ተካሄደዋል::

### 3.2.4 የወሳኝ ኩነቶች ምዝገባና ስታቲስቲክስን በተመለከተ

- ወደፊት በአገር አቀፍ ደረጃ የሚቋቋሙት የወሳኝ ኩነቶች ምዝገባና ስታቲስቲክስ ሥርዓቶች በሕግ፣ በቴክኒክ፣ በአስተዳደር፣ በበጀትና በሰው ኃይል ድልድል በኩል ሊያጋጥሙአቸው የሚችሉ ችግሮችን ለማጥናት የሚያስችል በተባበሩት መንግሥታት የሕጻናት መረጃ ድርጅት (UNICEF) የገንዘብና በጽ/ቤቱ የቴክኒክ ድጋፍ በደቡብ ኢትዮጵያ ብሔር ብሔረሰቦችና ሕዝቦች በአማራና በትግራይ ክልሎች ሞዴል የምዝገባና ስታቲስቲክስ ፕሮግራሞች የሥራ ሂደት ላይ በመስክ በመገኘት ግምገማ ተካሂዷል፡፡

- የሥነ ሕዝብና ጤና ጥናትን አስመልክቶ የተባበሩት መንግሥታት የሕዝብ ጉዳይ ፈንድ (UNFPA) ለለጋሽ አገሮችና ድርጅቶች በየጊዜው የሚቀርበው የሥራ ሂደት ሪፖርት ማዘጋጀት እና ሌሎች ተዛማጅ ተግባራት ተከናውኗል፡፡

- የዚህን ፕሮግራም አጠቃላይ ሂደት መከታተልና መገምገም እንዲቻል የሞዴል ፕሮግራሙ በሦስት ክልሎች ከተጀመረ ጊዜ ጀምሮ በቴክኒክ፣ በገንዘብ፣ በአስተዳደርና በአደረጃጀት፣ በሰው ኃይልና በአፈጻጸም ረገድ ያጋጠሙት ችግሮች ለመገምገም ከበጀት ዓመቱ መጀመሪያ ጀምሮ የቫይታል ስታቲስቲክስ የመምሪያው አባላት በተለያዩ ቡድኖች በመከፋፈል ከሰኔ 25/1997 እስከ ሐምሌ 1/1997 በደቡብ ኢትዮጵያ ብሔር ብሔረሰቦችና ሕዝቦች ክልል በ14 የገጠርና የከተማ ቀበሌዎች ፣ በአማራ ክልል ከሐምሌ 20 ቀን 1997 – ሐምሌ 29 ቀን 1997 በክልሉ ለሞዴል የምዝገባ ፕሮግራሙ ከተመረጡት 32 የገጠርና የከተማ ቀበሌዎች ውስጥ በ27ቱ የመስክ ጉብኝት ተደርጓል፡፡

- ከዚህም ሌላ ሁለት አባላት ያሉት ቡድን በትግራይ ክልል በተለያዩ ወረዳዎች በመካሄድ ላይ ያለውን ሞዴል የምዝገባና ስታቲስቲክስ ፕሮግራም በቴክኒክ፣ በአስተዳደርና በአፈጻጸም ረገድ ባጋጠሙት ችግሮችና የተገኙ ልምዶች በሚገመግም መስከረም 7 ቀን 1998 በመቀሌ ከተማ በተካሄደ ስብሰባ ላይ ተሳትፏል፡፡ በዚህም ወቅት በስብሰባው ላይ ቡድኑ በምዝገባ ቅጾቹ ላይ ስለተደረጉ ለውጦችና በሞዴል

ፕሮግራሙ ላይ ስለተሰራው የወሳኝ ኩነቶች ምዝገባ ኮምፒውተር ፕሮግራም ማብራሪያ ሰጥቷል፡፡

- በሦስቱም ክልሎች በተካሄዱ ጉብኝቶች ቡድኖች በመስክ በመገኘት ሥራውን ከሚያከናውኑ መዝገቢዎች፣ ከአስተባባሪዎችና ከየወረዳው ሥራ አስፈጻሚዎችና ከክልል የሥራ ኃላፊዎች ጋር በቴክኒካዊ፣ በአስተዳደራዊና የበጀት ጉዳዮች ላይ በመወያየት የክልልን ሞዴል የምዝገባና ስታቲስቲክስ ፕሮግራም በመገምገምና የፕሮግራሙን ደካማና ጠንካራ ጐኖች የመለየት ተግባራትን የሚዳስስ ሪፖርት አዘጋጅቶ ለሚመለከታቸው አካላት አቅርቧል፡፡

- ለሞዴል የወሳኝ ኩነቶች ምዝገባና ስታቲስቲክስ ፕሮግራሙና ወደፊት በአገር አቀፍ ደረጃ ለሚቋቋሙት የወሳኝ ኩነቶች ምዝገባና ስታቲስቲክስ ሥርዓቶች የሚያገለግሉ የምዝገባ አፈጻጸም /መዝጋቢዎች መመሪያ/ የልደት፣ የሞት፣ የጋብቻ ፍቺ የክብር መዝገቦችና የምስክር ወረቀቶችን የልደት፣ የሞት፣ የጋብቻና ፍቺ ኩነቶች ምዝገባና ስታቲስቲክስ ሥርዓቶች ሞዴል ፕሮግራም የአስተዳደርና የአደረጃጀት አፈጻጸም መመሪያ የልደት፣ የሞት፣ የጋብቻና ፍቺ ሥርዓቶችን በመቋቋም የምዝገባ ተቋማትና ዋንኛ ተባባሪ ድርጅቶች ዋና ዋና የተግባር ዘርፎች መመሪያ፣ አገር አቀፍ የድርጊት መርሃ ግብርን የማረምና የማሻሻል ተግባራት ተከናውነዋል፡፡

- ከተባበሩት መንግሥታት የሕፃናት መረጃ ድርጅት ጋር ተከታታይ ግንኙነት በማድረግ እ.ኤ.አ በ2005 በሦስት /ክልሎች በአማራ፣ በትግራይና በደቡብ ብሔር ብሔረሰቦችና ህዝቦች/ የተጀመረው የወሳኝ ኩነቶች ምዝገባና ስታቲስቲክስ ሞዴል ፕሮግራም በ2006 ለመቀጠል እንዲቻል ከክልሎቹ ጋር በመተባበር የፕሮጀክት ዶክመንት ተዘጋጅቶ ለድርጅቱ ቀርቧል፡፡ እንደዚሁም ሞዴል ፕሮግራሙን በሌሎች አዳዲስ ክልሎች ስለሚጀመርበት ሁኔታ ከድርጅቱ ጋር ምክክር ተደርጓል፡፡ በዚሁ መሠረት የኦሮሚያ ክልል በሞዴል ፕሮግራሙ እንዲታቀፍ ከክልሉ ፋይናንስ ኢኮኖሚ ልማት ቢሮ ለድርጅቱ የሚያቀርብ የፕሮጀክት ዶክመንት ለማዘጋጀት ለቢሮው የቴክኒክ እገዛ ተደርጓል፡፡

## 4. የ1998 በጀት ዓመት የፊዚካል ሥራ አፈጻጸም

በ1998 በጀት ዓመት መ/ቤቱ ለሚያካሂዳቸው አዳዲስ ጥናቶችንና ከ1997 የተሸጋገሩ ቀሪ ሥራዎችን ለማከናወን በዕቅድ መያዙንና በበጀት ዓመቱ ያከናወናቸውን ሥራዎች በዝርዝር ቀርበዋል፡፡ የእነዚህን ጥናቶች የፊዚካል አፈፃፀም በተመለከተ ደግሞ በሚቀጥለው ሠንጠረዥ ቀርቧል፡፡

ሠንጠረዥ 1 የ1998 በጀት ዓመት የዘጠኝ ወራት የፊዚካል ሥራ አፈጻጸም

| ተራ ቁ. | የጥናቱ ዓይነት | ጥናቱ የሚገኝበት ደረጃ | እስከ 1997 በጀት ዓመት መጨረሻ የተከናወነ | የዘጠኝ ወራት | | |
|---|---|---|---|---|---|---|
| | | | | ዕቅድ | ክንውን | አፈፃፀም |
| 1 | የ1998 የግብርና ናሙና ጥናት | | | | | |
| 1.1 | የሰብል ምርት ትንበያ ጥናት | አዲስ | 6.49 | 93.51 | 93.51 | 100 |
| 1.2 | የግብርና ምርት ናሙና ጥናት የመኸር ወቅት | | | | | |
| | • የታረሰ መሬት ናሙና ጥናት | አዲስ | 6.49 | 93.51 | 83.51 | 89 |
| | • የእርሻ ሥራ አጠቃላይ ሁኔታ | አዲስ | 6.49 | 91.29 | 81.29 | 89 |
| | • የመሬት አጠቃቀም | አዲስ | 6.49 | 91.29 | 81.29 | 89 |
| 1.3 | የቤት እንስሳት ዶሮና የንብ ቀፎዎች ጥናት | አዲስ | 6.43 | 93.57 | 85.57 | 91 |
| 1.4 | የግብርና ምርት ናሙና ጥናት የበልግ ወቅት | አዲስ | 6.43 | 8.51 | 8.51 | 100 |
| 1.5 | የሰፋፊና መካከለኛ የድርጅት እርሻዎች ጥናት | አዲስ | 6.43 | 67.88 | 8.51 | 13 |
| 1.6 | የ1997 የግብርና ምርት ናሙና ጥናት በበልግ ወቅት | ነባር | 65.00 | 35.00 | 35.00 | 100 |
| 1.7 | የ1997 የሰፋፊና መካከለኛ የድርጅት እርሻዎች ጥናት | ነባር | 65.00 | 35.00 | 25.00 | 71 |
| 2 | የግብርና ውጤቶች የአምራቾች ዋጋ ጥናት | አዲስ | 3.00 | 74.71 | 74.71 | 100 |
| 3 | የችርቻሮ ዋጋ ጥናት | አዲስ | 3.00 | 75.77 | 75.77 | 100 |
| 4 | የኢኮኖሚና ማህበራዊ ደህንነት ጥናት | ነባር | 90.00 | 10.00 | 10.00 | 100 |
| 5 | የቤተሰብ ገቢ፣ ፍጆታና ወጪ ጥናት | ነባር | 65.00 | 35.00 | 20.00 | 57 |
| 6 | ዓለም አቀፍ የንጽጽር ፕሮግራም በአፍሪካ | ነባር | 6.36 | 66.21 | 51.00 | 77 |
| 7 | ወቅታዊ የማምረቻ፣ የንግድና የአገ.ሰጪ. ድርጅት | አዲስ | - | 84.64 | 84.64 | 100 |
| 8 | የማምረቻ ኢንዱስትሪ የምርት ዋጋ ኢንዴክስ | አዲስ | 15.00 | 63.75 | 63.75 | 100 |
| 9 | የአነስተኛ ማምረቻ አንዱስትሪ ጥናት | አዲስ | - | 90.00 | 60.00 | 67 |
| 10 | የ1997 የትላልቅና መካከለኛ ማምረቻ ኢንዱ ጥናት | አዲስ | - | 66.20 | 15.00 | 23 |
| 11 | የማዕድንና ቁፋሮ ጥናት | አዲስ | - | 14.52 | 14.52 | 100 |
| 12 | የኮንስትራክሽን ጥገና | አዲስ | - | 60.00 | 15.00 | 25 |
| 13 | የ1996 የትላልቅና መካከለኛ ማምረቻ ኢንዱ. ጥናት | ነባር | 65.00 | 35.00 | 35.00 | 100 |
| 14 | የ1997 የሰው ኃይል ጥናት | ነባር | 65.00 | 35.00 | 20.00 | 57 |
| 15 | ለኤች.አይ.ቪ. በምክንያት የሚጠቀሱ ባህርያት ጥናት | ነባር | 65.00 | 35.00 | 20.00 | 57 |
| 16 | ተከታታይ የሥራ ስምሪት ጥናት | አዲስ | - | 47.81 | 15.00 | 31 |

## 5. ሜቶዶሎጂ አገልግሎት

### 5.1 የሳምፕሊንግ ሜቶዶሎጂን በተመለከተ

- የ1997 የሰው ኃይል ጥናትን በሚመለከት ለማባዣ የሚያገለግሉ በየቆጠራው ቦታ የተመዘገቡ ቤተሰቦች ብዛት ከየቆጠራ ቦታው የመልቀም ሥራ ተካሂዶ የ Weight እና Rate ፎርማት ተዘጋጅቶ በየቆጠራ ቦታው የተለቀሙትን ቤተሰቦች ብዛት ወደ ኮምፒውተር የማስገባቱ ሥራ ተጠናቋል።

- የ1997 ዓ.ም የበልግ ወቅት ግብርና ናሙና ጥናት፣ ለመሬት ስፋትና ምርት መጠን ጥናት፣ ለእርሻ ሥራ ሁኔታ ጥናት Weight እና Rate ዝግጅት እንዲሁም የናሙና ጥናቱ አስተማማኝነት ግምገማና የሜቶዶሎጂ ሪፖርት ዝግጅት ሥራ ተጠናቋል።

- የ1998 ዓ.ም የግብርና ናሙና ጥናት የናሙና ቆጠራ ቦታዎችንና የሠፈራ መንደሮችን ዝርዝር የያዘ ኮድ ቡክ ተዘጋጅቶ ለሚመለከታቸው ተሠራጭቷል።

- ለ1998 ግብርና ናሙና ጥናትና ለ1997 ዓ.ም የሰው ኃይል ጥናት የአካባቢ መለያን በሚመለከት ለኤዲተሮችና ኮደሮች ሥልጠና ተሰጥቷል።

- በኢኮኖሚያዊ ድርጅቶች ቆጠራ ወቅት ከመረጃ ማቀነባበሪያ የተገኙ የቆጠራ ቦታዎችን ዝርዝር ከካርቶግራፊ ክፍል ካለው ካርታና መግለጫ ካላቸው የቆጠራ ቦታዎች ዝርዝር ጋር እንዲገናዘብና ልዩነቶች እንዲለቀሙ የማድረግ ሥራ ተካሄዷል።

- ለ1998 ዓ.ም ተከታታይ ሥራ ስምሪት ጥናት የአመዘጋገብና የአመራረጥ መመሪያ ተዘጋጅቶ ለሚመለከተው የተላለፈ ሲሆን፣ የናሙና ምርጫና የቆጠራ ቦታ ካርታ ዝግጅት ተደርጓል።

- የ1998 ዓ.ም የአነስተኛ ማምረቻ፣ አገልግሎት ሰጭ ድርጅቶችና የምግብ ዋስትና ጥናቶች የሳምፕሊንግ ዲዛይንና የድርጅቶች አመዘጋገብና አመራረጥ መመሪያ ዝግጅት ሥራ ተጠናቋል። በከተሞች የሚጠኑ ድርጅቶችን

የመምረጥ ሥራ የተከናወነ ሲሆን፣ ስለድርጅቶቹ አመዘጋገብ መምሪያ ተዘጋጅቶ ሥልጠናው ተሰጥቷል፡፡ እንዲሁም ለመስክ ሥራና ለኤዲቲንግና ኮዲንግ የሚያስፈልገውን ኮድ ቡክ የማዘጋጀቱ ሥራ ተጠናቋል፡፡

- የ1998 የገበያ መረጃ ሥርዓት ጥናት የሳምፕሊንግ ዲዛይንና የናሙና መረጣ ሥራ ተከናውኗል፡፡ እንዲሁም የ1997 ዓ.ም የትላልቅና መካከለኛ አርሻዎች ጥናት የአካባቢ መለያ ኮድ የኤዲትንግና የኮዲንግ ተግባር ተካሄዷል፡፡

- የ1997 ዓ.ም ኤች አይ ቪ/ ኤድስ ባህሪ ቅኝት ጥናትን በሚመለከት የተማሪዎችን Weight እና Rate ለማዘጋጀት የሚያስፈልግ የፎርማት ዝግጅት ሥራና የ Weight እና Rate ዝግጅት ሥራም ሙሉ በሙሉ ተጠናቋል፡፡

- የ1998 የሰብል ትንበያ ጥናት Weight እና Rate የተዘጋጀ ሲሆን የሜቶዶሎጂ ሪፖርት ዝግጅትም ተጠናቋል፡፡

- የቡድኑን የወደፊት ሥራ ጥራቱን የጠበቀና አንድ ወጥ የሆነ ለማድረግ ይቻል ዘንድ አጠቃላይ የሥራ የአሠራር ሁኔታ የሚያሳይ ፍሎው ቻርት በየደረጃው የሚከናወኑ ተግባራትና የእያንዳንዱ ባልደረባ ተግባርና ኃላፊነትና የአሠራር ስታንዳርድ የሚገልጽ መመሪያ ተዘጋጅቷል፡፡

- የ1998 ዓ.ም የቤት እንስሳት ናሙና ጥናት Weight እና Rate ዝግጅት ሥራን በማጠናቀቅ በኤዲቲንግና ኮዲንግ ሥራ ወቅትም የአካባቢ መለያን በሚመለከት ክትትል በማድረግ የእርምት ሥራ ተካሄዷል፡፡ እንዲሁም የውጤት አስተማማኝነት ግምገማ ተከናውኖና ሪፖርቱ ተዘጋጅቶ ለሚመለከተው አካል ተላልፏል፡፡

- የ1998 ተከታታይ የሥራ ስምሪት ጥናትን በሚመለከት ቀደም ሲል የተመረጡ ናሙናዎችን በአዲሱ የቀበሌ አደረጃጀት መሠረት የማስተካከልና የ526 የቆጠራ ቦታ ካርታዎች ዝግጅት ተጠናቆ ለየቅ/ጽ/ቤቶች ተሠራጭተዋል፡፡ በተጨማሪም የቤተሰቦች አመዘጋገብና አመራረጥ መመሪያ ተዘጋጅቶ ሥልጠናው ተሰጥቷል፡፡

- በየወረዳው ባሉ ገበሬ ማህበራት የሚገኙ ቤተሰቦችን ብዛት የማጠናቀር ሥራም የተከናወነ ሲሆን፣ ለ1998 ዓ.ም የታረሰ መሬት ስፋትና የተገኘ ምርት መጠን በሁለት ዓይነት አማራጮች Weight እና Rate የማዘጋጀት ሥራ በማካሄድ ላይ ይገኛል።

- ለ1999 ዓ.ም ህዝብና ቤቶች ቆጠራ የሙከራ ጥናት የሚያስፈልጉ የናሙናዎችን ብዛት በየከተማውና ወረዳው የመምረጥ ሥራ ተጠናቋል። እንዲሁም የቤተሰቦች መመዝገቢያ በቆጠራ ቦታ ደረጃ የሚጠየቁ ጥያቄዎችንና በዋናው መጠይቅ የሚካተቱ ሁለት ምዕራፎችን አጠቃላይ ይዘት ቅጾችን፣ በማዘጋጀትና የመጠይቆች የአሞላል መመሪያ ዝግጅት በአብዛኛው ተከናውኗል።

## 5.2 ስታንዳርድና መዛግብት አያያዝን በተመለከተ

- ለወረዳ ኔት ፕሮግራም የተሰበሰቡ ፎርማቶች ጽንሰ ሃሳቦችና ፍችዎቻቸውን በየዘርፉ በመተንተን ትርጉማቸው በግልጽ የተቀመጡትንና ያልተቀመጡትን የመለየት ሥራ ተከናውኗል።

- የሥራ ምደባዎችን በየመምሪያዎቹ ለሚያከናውኑት አይዚክ /ISIC/ ጋር ለማነፃፀር የመጀመሪያ ረቂቅ ዶክመንት በመዘጋጀት ላይ ይገኛል።

- አጠቃላይ በስታንዳርድ ደረጃ ሊያገለግሉ የሚችሉ ጽንሰ ሃሳብና ፍችዎቻቸው የማዘጋጀቱ ሥራ ተከናወኗል።

## 5.3 ካርቶግራፊን በተመለከተ

- ከተለያዩ መ/ቤቶች የከተሞችን ማስተር ፕላን በትወስት በማምጣት የ42 ከተሞች ማስተር ፕላን 44 ኮፒ የተዘጋጀ ሲሆን፣ የወረዳ ካርታዎች ኮፒ ታትመው ለዲጂታይዚንግ ተዘጋጅተዋል። እንዲሁም የ221 ወረዳ የቆጠራ ካርታዎችና ተዛማጅ ዶክመንቶች ርክክብ ተፈጽሟል።

- የቆጠራ ካርታ የሚያስፈልጋቸውን ቀሪ ወረዳዎች በመለየትና የሚሸፍናቸው የቶፖግራፊ ካርታ በማዘጋጀት የ47 ወረዳ ካርታዎች ለሚመለከታቸው ጽ/ቤቶች ተልከዋል::

- ከመስክ ተጠናቀው የተላኩ የቤተሰብ ምዝገባና የኮኦርዲኔቶች ዝርዝር በተዘጋጀው የዳታ ኢንትሪ ፕሮግራም መሠረት በኮምፒውተር የመቅረጽ ተግባር ተከናውኗል::

- በGIS በመታገዝ የቆጠራውን ውጤት ለተጠቃሚ ለማቅረብ የ12 ወረዳዎች ካርታ በቀጣይነት ዲጂታይዝድ የማድረግ ሥራዎችና የገጠርና የከተማ የቤተሰብ መመዝገቢያ ቅጾች /ገ-2 እና ከ-2/ና የድንበርና የውስጥ ገጽታዎች መመዝገበያ ቅጽ /ገ-6/ መረጃዎችን ኤዲትና ኮድ በማድረግ የ10 ወረዳዎች በኮምፒውተር የመቅረጽ ሥራዎችና ሌሎች ተዛማጅ ሥራዎች ተከናውኗል::

- በ1998 ዓ.ም ለሚካሄደው የግብርና ናሙና ጥናት አዲስ ለተመረጡና ካርታቸው ለጠፋ የቆጠራ ቦታዎች ካርታ ተዘጋጅቷል:: ለተለያዩ ጥናቶች የ622 ቆጠራ ቦታዎች ካርታ ኮፒ ተደርጐ ለሚመለከተው ክፍል ተሰጥቷል::

- በስምንት ዞኖች ለሕዝብና ቤት ቆጠራ ሥራ የሚያገለግሉ ባለ 1:50,000 መስፈርት የቶፖግራፊ ካርታዎችን በመለየት ተገዝተው ለሚመለከታቸው ቅ/ጽ/ቤቶች ተሠራጭተዋል:: እንዲሁም 173 የወረዳ ካርታዎች ለውጭ ተገልጋዮች ተሸጠዋል::

## 6. መረጃ ማቀነባበርን በተመለከተ

### 6.1 የኤዲቲንግና ኮደንግና ዳታ ኢንትሪ

በዕቅድ ዘመኑ ዘጠኝ ወራት ውስጥ የመረጃ ማሰባሰቡ ተግባር የተጠናቀቀላቸው የ1996 የትላልቅና መካከለኛ ማምረቻ ኢንዱስትሪ ጥናት፣ የ1997 የበልግ ጥናት፣ የቤተሰብ ገቢ ፍጆታና ወጪ ጥናት፣ የሰው ኃይል ጥናት፣ የመጀመሪያ ሩብ ዓመት ወቅታዊ ጥናት፣ የ1998 የሰብል ትንበያ ጥናትና የሰብል ሁኔታ ግምገማ ጥናት፣ የሰፈራ ጣቢያዎች የሰብል ትንበያ ጥናት፣ የቋሚ ሰብል ጥናት የኤች.አይ.ቪ. /ኤድስ የባህሪ ቅኝት ጥናት፣ የጥቅምትና የህዳር ወር ICP ጥናትና እንዲሁም የተሰበሰቡ መረጃዎች ወርሃዊ የዋጋ ጥናቶች የ1998 የቋሚ ሰብል ጥናት፣ የሳተላይት ጥናት፣ በመኸር ወቅት ግብርና የሰብል አጨዳ ጥናት፣ የሁለተኛ ሩብ ዓመት የወቅታዊ ጥናት፣ ከታህሣሥ እስከ የካቲት ICP ጥናት ከዳታ ኤዲቲንግ ኮዲንግ እስከ ዳታ ኢንትሪና ክሊኒንግ ድረስ ተጠናቋል፡፡ የ1998 የቤት እንስሳት ጥናት፣ የምግብ ዋስትና ጥናት፣ የ1997 ሰፋፊና መካከለኛ እርሻዎች ጥናት፣ የቋሚ ሰብል ጥናት፣ የሰፋፊና መካከለኛ እርሻዎች ጥናት የኤዲቲንግና ኮዲንግ ሥራ ተጠናቆ ለዳታ አንትሪና ክሊኒንግ ሥራ ዝግጁ ሆነዋል፡፡

### 6.2 የሠንጠረዥ ዝግጅት

- የመረጃ ማሰባሰቡ ተግባራት የተከናወነላቸው ወርሃዊ የዋጋ ጥናቶች የኢንዴክስ መረጃ፣ የ1997 የቤተሰብ ገቢ ፍጆታና ወጪ ጥናት፣ የ1996 የበልግ ጥናት፣ የታረሰ መሬት ስፋትና የምርት መጠን ጥናት፣ የ1997 የመሬት አጠቃቀም የእርሻ ሥራ ሁኔታ ጥናት፣ እንዲሁም የ1998 የመጀመሪያ ሩብ ዓመት የወቅታዊ ጥናት፣ የ1996 የትላልቅና መካከለኛ ኢንዱስትሪዎች ጥናትና፣ የ1997 የሰው ኃይል ጥናት፣ የሰፋፊና መካከለኛ እርሻዎች ጥናት፣ 1998 የሰብል ትንበያ ጥናት፣ የሁለተኛ ሩብ ዓመት የወቅታዊ ጥናት፣ ስለ ኤች አይ ቪ የባህሪ ጥናት፣ የተማሪዎች መጠይቅ ሠንጠረዦች ተዘጋጅተዋል፡፡

- በሌላ በኩል መረጃዎችን ወደ SPSS Format በመለወጥ ለተጠቃሚዎች በሚያመች መንገድ ለማዘጋጀት በታቀደው መሠረት የ1996 የኢኮኖሚና ማህበራዊ ደህንነት ጥናት፣ የ1997 አጠቃላይ የእርሻ ሥራ ሁኔታ ጥናት፣

የ1997 የታረሰ መሬትና የምርት መጠን ጥናት፣ የ1997 የመሬት አጠቃቀም ጥናት፣ የበልግ ወቅት ጥናት፣ የ1997 የአምራቾች ዋጋ ጥናት፣ የ1996 የትላልቅና መካከለኛ ኢንዱስትሪ ጥናት፣የ1997 የአምራቶች ዋጋ ጥናት፣ የ1997 የሆቴሎች ዋጋ ጥናትና የቤት እንስሳት ጥናት፣ ከ1988-1993 ያለው የቤት እንስሳት ጥናት መረጃዎችን ወደ SPSS Format የመለወጥ ሥራ ተጠናቋል።

6.3 ሌሎች የተከናወኑ ተግባራት

- በመ/ቤቶች፣ በድርጅትና በግለሰብ ደረጃ ለቀረቡ የመረጃ ጥያቄዎች ምላሽ ተሰጥቷል።

- እ.ኤ.አ የ2005 የሩብ ዓመት የትላልቅና መካከለኛ ኢንዱስትሪዎች ጥናት Indicators በEthio Info Data Base ሥራ ተጠናቋል።

- እ.ኤ.አ የ2000 Demography and Health Survey (DHS) መረጃ መሬት ስፋትና የምርት መጠን ጥናት መረጃ አመልካች በEthio Info Data Base የማዘጋጀቱ ሥራ ተጠናቋል። እ.ኤ.አ የ2004 እና የ2005 የታረሰ መሬት ስፋትና የምርት መጠን ጥናት መረጃ አመልካች፣ የ1996 እና የ1997 የሕዝብ ብዛትና አሠፋፈር ሁኔታ አመልካች በEthio Info Data Base የማዘጋጀቱ ሥራ ተጠናቋል።

## 7. ኢንፎርሜሽን ኮሙኒኬሽን ቴክኖሎጂን በተመለከተ

- በዕቅድ ዘመኑ ዘጠኝ ወራት ውስጥ ለICT አቅም ግንባታ ከUNDP ተገዝተው የመጡ ዕቃዎችን አስፈላጊውን የኮንፊገሬሽን ሥራ በመሥራት ዕቃዎችን በመረከብ ሥራ ላይ እንዲውሉ ተደርገዋል።

- የመ/ቤቱ ድረ-ገጽ ተጠናቆና ተመርቆ ሥራ ላይ የዋለ ሲሆን በዚሁ ድረ-ገጽ መ/ቤቱ ውስጥ ባለው Server Host በማድረግ በየትኛውም ዓለም ያለ ተጠቃሚ እንዲያገኘው የሚያስችለውን የDomain Registration እና Public IP ከኢትዮጵያ ቴሌኮሙኒኬሽን በመግዛት ጥቅም ላይ እንዲውል ተደርጓል። በመ/ቤቱ

ኔትወርክ የተገናኘላቸው የሚመለከታቸው የመ/ቤቱ ባለሙያዎችም Official e-mail አካውንት እንዲያገኙ ተደርጓል::

- በማዕከላዊ የመረጃ ማዕከል ተከማችተው ከነበሩ ጥናቶች ውስጥ የ1996፣ 1998፣ 2002፣ 2004፣ የኢኮኖሚና የማህበራዊ ደህንነት ጥናቶች የሁለት ዓመት የቤተሰብ ገቢ ፍጆታና ወጪ ጥናቶችን የሥራ ስምሪት ጥናት፣የትላልቅና የመካከለኛ ኢንዱስትሪ ጥናቶች፣ እንዲሁም የ2004 የግብርና ጥናት የመሬት ስፋትና ምርት መጠንና የናሙና ጥናቶችን የሚመለከት በጠቅላላው ከ2150 በላይ የሆኑ ከተለያዩ ጥናቶች ጋር ተያያዥነት ያላቸው ፋይሎችና 36 የሚሆኑ የተለያዩ ጥናቶችና የሦስት ዓመት ዓመታዊ የስታቲስቲክስ መጽሔቶች የData Management Toolkit በመጠቀም ለተጠቃሚዎች አመች በሆነ የማሠራጫ መንገድ ተደራጅተው እንዲቀመጡ ተደርጓል::

- የመ/ቤቱን የሰው ኃይል መረጃ አያያዝ ሥርዓት ዘመናዊ አሠራርን የተከተለ እንዲሆን ወደ ኮምፒውተር የማስገባት ሥራ በማከናወን ለፐርሶኔል ክፍል ሙያዊ እገዛ ተደርጓል::

- ብዛት ያላቸውን ኮምፒውተሮች መለዋወጫን የመቀየር ሥራ፣ የኮንፊገሬሽን ሥራ እንዲሁም የ38 የኮምፒውተር ጥገናና Memories የመጨመር ተግባራት ተከናውነዋል::

- የServer ክፍሉ ደረጃውን የጠበቀ ለማድረግ የሚያስፈልጉ ዕቃዎችን ዝርዝር በማቅረብ ከሚመለከታቸው ጋር በመመካከር የዕቃ መረጣና ግዥው ተካሄዶ ዕቃዎቹን በማሟላት ደረጃውን የጠበቀ እንዲሆን ተደርጓል::

- የመ/ቤቱን የመረጃ ክምችትና ስርጭት እንዲሁም የኔት ዎርክ አስተዳደር በተቀላጠፈ መንገድ ለማካሄድ እገዛ የሚያደርግ የአንድ ሳምንት ሥልጠና ከውጭ በመጡ ባለሙያዎች የተሰጠ ሲሆን 76 ተጨማሪ ኔትወርትክ በመ/ቤቱ በተለያዩ ቢሮዎች ተዘርግተዋል::

- የጂኦግራፊ ኢንፎርሜሽን ሲስተም የቅድመ ዝግጅት ሥራዎችን በማካሄድ በቆጠራ ካርታ ሥራ በGPS አማካይነት ተጠናቅረው የመጡ መረጃዎች የዳታ

ቤዝ (Data Base) ምሥረታ በመከናወን ላይ ይገኛል። እንደዚሁም የ2004 የኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ ደህንነት ጥናቶችን በመጠቀም የመጀመሪያ ደረጃ ትንተና ሥራ ተካሄዷል። በተጨማሪም የመረጃ ክምችት ሲስተሙን ለመቀየር በሚደረገው ጥረት የኢንዱስትሪ ጥናትን መሠረት በማድረግ የData Base ምሥረታ ተጀምሯል።

- በመ/ቤቱ ድረ-ገጽ ላይ ወቅታዊ የሆኑ መረጃዎች እንዲካተት የተደረገ ሲሆን የመ/ቤቱን አቅም ለመገምባት ከዓለም ባንክ በኩል ለሚከናወኑት ከ Trust Fund እና STATCAP ድጋፍ ለማስገኘት የሚረዳ ዶኩመንት በማዘጋጀት ለሚመለከተው ቀርቧል።

- ከተለያዩ ድርጅቶች የቀረቡትን የመረጃን በኤሌክሮኒክስ ፎርማት የማግኘት ጥያቄዎች ተስተናግደዋል።

## 8 ሲቪል ሰርቪስ ማሻሻያ ጽ/ቤት

### ሀ. ልዩ ልዩ ተግባራትን በተመለከተ

- የመ/ቤቱ ተልዕኮ የተሳካ እንዲሆን እስካሁን ድረስ በተደረጉት ጥረቶች በመ/ቤቱ ድረ-ገጽ ልዩ ልዩ ጠቀሜታ ያላቸውን ስታቲስቲካዊ መረጃዎች በኢንተርኔት የማሠራጨት ሥራ እንዲጀመር ተደርጓል። በዚህም መ/ቤቱ በዕቅድ ዘመኑ የሚያካሂዳቸውን ዋና ዋና የጥናት ዓይነቶች የነዚህን የጥናት ውጤቶች መረጃ መቸና እንዴት እንደሚገኝ ስለመረጃዎቹም የትኛውን የሥራ ክፍል ማነጋገር እንዳለባቸው ኢንተርኔቱ ገለፃ የሚሰጥ በመሆኑ ተጠቃሚው ወደ መሥሪያ ቤት ሳይመጣ በቀላሉ ባለበት ቦታ ሆኖ መረጃዎችን እንዲያገኝ አስችሎታል። በተጨማሪም በዩኒሴፍ ቴክኒካዊ እርዳታ Ethio Info የተባለውን ሶፍት ዌር ከመረጃ መረቡ ጋር በማገናኘት ለምዕተ ዓመቱ የልማት ግቦች ጠቋሚ መረጃዎችን ለተጠቃሚዎች በቀላሉ እንዲያገኙ አስችሏል።

- የመረጃ ዴስክ የሥራ ክፍል 526 የውጭ ተገልጋዮችን በመቀበልና 5,049 ኢትዮጵያውያንን በማስተናገድ ከቤተ መጻሕፍቱ፣ ከሚመለከታቸው

የሥራ ክፍሎችና ባለሙያዎች ጋር በማገናኘት አገልግሎቱን በቀላሉ እንዲያገኙ አስችሏል።

- ቤተመጻሕፍቱ የውስጥና የውጭ ተገልጋዮች ባቀረቧቸው ጥያቄዎች መሠረት ልዩ ልዩ መጻሕፍትን ለመግዛት ዝግጅቱ የተጠናቀቀ ሲሆን፣ በቤተ መጻፍቱ ውስጥ የፎቶ ኮፒ አገልግሎት በመጀመሩ ተገልጋዮች የሚፈልጓቸውን መረጃዎች ብቻ ኮፒ በማድረግ እንዲወስዱ በማስቻሉ ቀልጣፋ አገልግሎት ከማግኘታቸውም ባሻገር ሙሉ ሪፖርቱን ለመግዛት ከሚያወጡት ወጪ ነፃ ሆነዋል።

- የሠራተኛውን የመፈጸም አቅም ለማጐልበት ሁለት የኦዲት አገልግሎት ሠራተኞች በውስጥ ኦዲት አሠራር ላይ በኢትዮጵያ ሥራ አመራር አንስቲትዩት፣ ሦስት ሠራተኞች ደግሞ በገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ሚኒስቴር እንዲሰለጥኑ ተደርጓል፣ 11 ከልዩ ልዩ የሥራ ክፍሎች የተውጣጡ ሠራተኞች በኮምፒውተር መሠረታዊ አጠቃቀም ማለትም በWord, Excell እና Access በግል ተቋም የሰለጠኑ ሲሆን አምስት ባለሙያዎች በአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ፣ 10 ባለሙያዎች ደግሞ በውጭ ሀገር ለማስተርስ ዲግሪ እየሰለጠኑ ይገኛሉ።

- መ/ቤቱ ለሥራ አመች የሆነ አደረጃጀት እንዲኖረው ለማድረግ በአዲሱ ድርጅታዊ መዋቅርና የሰው ኃይል ፍላጐት መሠረት የፌዴራል ሲቪል ሰርቪስ ኤጀንሲ የሰው ሃብትና ሥራ አመራር መምሪያንና የፋይናንስ መምሪያን የሥራ መደቦች በተፈለገው ደረጃ አጽድቆ የመለሰ ሲሆን፣ የቴክኒክና ንብረት አስተዳደር አገልግሎትን በሚመለከት ደረጃው ዝቅ ብሎ በመመደቡ እንደገና እንዲታይ ጥያቄ ለኤጀንሲው ቀርቧል። በሌላ በኩል በተፈቀዱት የሥራ መደቦች የሰው ኃይል ለመመደብ ዝግጅት እየተደረገ ነው።

- ስለ መኪና አጠቃቀምና ጥገና በፋይናንስ አጠቃቀምና ወጪ ማስረጃ አቀራረብ፣ ንብረት አስተዳደር፣ ስለ ፐርሶኔል ሥራዎች አፈጻጸም፣ ስለመረጃ ጥራትና ቁጥጥር በመሳሰሉት ጉዳዮች ላይ ማኔጅመንቱ ከ25 ቅ/ጽ/ቤቶች ኃላፊዎች ጋር ተወያይቶ አስተዳደራዊ ውሳኔ ሰጥቷል።

ሰ. <u>መሠረታዊ የአሠራር ማሻሻያ ሥርዓት /BPR/ ጥናትን በተመለከተ</u>

- ከመስከረም 1997 ዓ.ም ጀምሮ በመ/ቤቱ በአጭር ጊዜ ወስጥ የአሠራር ማሻሻያ በማድረግ ተገልጋዮችን በበለጠ ማርካት ይቻላል ተብሎ የታመነባቸውን ሁለት የሥራ ዘርፎች ማለትም የግብርና ስታቲስቲክስንና የመረጃ ክምችትና ስርጭትን በመምረጥ የBPR ሥራ ተጀምሯል፡፡

- የመ/ቤቱ የስታቲስቲክስ መረጃ ክምችትና ስርጭት የአሠራርና የአገልግሎት ማሻሻያ ሥርዓት ጥናትን በሚመለከት የመጨረሻ ምዕራፍ በሆነው ማለትም በመርሃ ግብሩ ላይ ከበላይ አስተባባሪና ገምጋሚ ኮሚቴ ጋር ውይይት ተደርጐበት በአሁኑ ሰዓት በተቀየሰው ማሻሻያ መሠረት በመተግበር ላይ ይገኛል፡፡

- የግብርና ስታቲስቲክስን መረጃ አቅርቦት የአሠራር ማሻሻያ ሥርዓት ጥናትን በሚመለከት በሥራ ክፍሉ የነበሩትን ችግሮች የመለየትና የመፍትሄዎችን የመቀየስ እንዲሁም ለማሻሻያው ተግባር መርሃ ግብር የማዘጋጀቱ ሥራ ተከናውነዋል፡፡ በተከናወኑ ሥራዎችም ላይ የበላይ ኃላፊዎች ከሚመለከታቸው ጋር ውይይት የተደረገባቸው ሲሆን፣ ቀሪው ተግባር ለበላይ አስተባባሪና ገምጋሚ ኮሚቴ አቅርቦ አስተያየት እንዲሰጥበት የማድረግ ሥራ ነው፡፡

- በተመሳሳይ ሌሎች የሥራ ዘርፎችና ክፍሎች ከላይ በተጠቀሱት ሁለት የሥራ ዘርፎች የተዘጋጁትን ማሻሻያዎች በሞዴልነት በመጠቀም የየራሳቸውን BPR እየሰሩ ለመ/ቤቱ የበላይ ሥራ አመራር ኮሚቴ በማቅረብ እያጸደቁ ይገኛሉ፡፡ በኤጀንሲው ከሚገኙት 19 የመምሪያና የአገልግሎት ክፍሎች መካከል አንድ መምሪያ ማሻሻያውን በመተግበር ደረጃ ላይ ያለ ሲሆን፤ አንድ መምሪያ ደግሞ ሁሉንም የጥናት ሂደት ደረጃዎች አጠናቆ ማሻሻያውን ለመተግበር በዝግጅት ላይ ነው፡፡ ከቀሪዎቹ 17 መምሪያዎችና አገልግሎቶች መካከል 13ቱ የአሰራር ማሻሻያ ጥናት ውጤቶች የሚተገበሩበት መርሃ ግብሮች በማዘጋጀት ደረጃ፣ አንድ መምሪያ የአሰራር ማሻሻያ በመቀየስ ደረጃ እና ሌላ አንድ ደግሞ የመምሪያውን ችግሮች በመለየት ደረጃ ላይ የሚገኙ ሲሆን በቀድሞው ሕዝብና ቤቶች ቆጠራ ኮሚሽን ስር የነበሩ ሁለት መምሪያዎች የማሻሻያ ጥናቱን እንዲጀምሩ ለማድረግ ታስቧል፡፡

## 9. የማስታወቂያና ሕዝብ ግንኙነት አገልግሎት

- በ1998 የዕቅድ ዘመን ዘጠኝ ወራት ውስጥ በመ/ቤቱ የተዘጋጁ 7,563 ልዩ ልዩ የጥናት ሪፖርቶች ለመንግሥት፣ ለዓለም አቀፍ ድርጅቶች፣ ለከፍተኛ ትምህርት ተቋማትና ለምርምር ማዕከላት በነፃ ተሠራጭተዋል፡፡ እንዲሁም 2,310 ልዩ ልዩ የጥናት ሪፖርቶችና የስታቲስቲክስ መጽሔቶች በብር 55,272.70 ሽያጭ ተፈጽሟል፡፡ እንዲሁም ብር 17,760 የአገልግሎት ዋጋ በማስከፈል ጥሬና የተቀነባበሩ መረጃዎች ለተጠቃሚዎች የተሸጡ ሲሆን፤ በዘጠኝ ወራት ውስጥ በጠቅላላው ከሽያጭና ከአገልግሎት ክፍያ ብር 73,032.70 ለመንግሥት ገቢ ተደርጓል፡፡

- የመ/ቤቱ ልሳን የሆነው ልሳን ማስኤ ቅጽ 4 ቁጥር 5 መጽሔት 2,000 ኮፒ፣ እንዲሁም ዜና ማስኤ ቅጽ 3 ቁጥር 4 1,500 ኮፒ ታትሞ የተሠራጨ ሲሆን ዜና ማስኤ ቅጽ 4 ቁጥር 2 ዝግጅት ተጠናቋል፡፡

- የመ/ቤቱን የ1997 የዕቅድ አፈጻጸም የመ/ቤቱን የ5 ዓመት የትኩረት አቅጣጫና ድረ-ገጽ ግንባታ፣ በመ/ቤቱ የተካሄደውን የኢኮኖሚና ማህበራዊ ደህንነት ጥናት፣ አገር አቀፍ የቤት እንስሳት ናሙና ቆጠራን፣ የአፍሪካ ስታቲስቲክስ ቀንን አላማና በዓል አከባበር፣ የመ/ቤቱን አጠቃላይ የሥራ እንቅስቃሴና የመረጃዎችን ጠቀሜታ፣ የሁለተኛውን ዙር የሥነ ሕዝብና ጤና ጥናት /DHS/ የመጀመሪያ ደረጃ ሪፖርት መጠናቀቅና የተገኘውን ውጤት፣ ዓለም አቀፍ የንጽጽር መርሃ ግብር ለአፍሪካ ጥናትና የሦስተኛው ዙር የሕዝብና ቤቶች ቆጠራ የቅድመ ዝግጅት ሥራዎችን በተመለከተ በሚመለከታቸው የሥራ ኃላፊዎች ጋዜጣዊ መግለጫ ተሰጥቷል፣ እንዲሁም ሌሎች በመ/ቤቱ የተከናወኑ ተግባራት በሬዲዮ፣ በቴሌቪዥንና በጋዜጦች ሽፋን እንዲያገኙ በማድረግ ለሕብረተሰቡ ግንዛቤን ለማስጨበጥ ተሞክሯል፡፡

- የመ/ቤቱ ቤተ መጻሕፍት ለመሥሪያ ቤቱ ሠራተኛና ከውጭ ለሚመጡ ተገልጋዮችና ተጠቃሚዎች ያልተቋረጠ የንባብ፣ የመረጃ አቅርቦትና የትውስት አገልግሎት በመስጠት ላይ ይገኛል፡፡

- በ1998 የዕቅድ ዘመን ዘጠኝ ወራት ውስጥ 245 የመ/ቤቱን ሪፖርቶች በመረከብና 94 ልዩ ልዩ አዳዲስ የውጭና የአገር ውስጥ ሕትመቶችን በልውውጥና በስጦታ በማሰባሰብ ቤተ መጻሕፍቱን ለማጠናከር ጥረት ተደርጓል፡፡
- በሌላ በኩል በቤተ መጻሕፍቱ ውስጥ ለውጭ ተገልጋዮች የፎቶ ኮፒ አገልግሎት በመስጠት ብር 1,307 ለመንግሥት ገቢ ሊሆን ችሏል፡፡
- የ1998 አዲስ ዓመትን ምክንያት በማድረግ 6,000 የግድግዳና 6,000 የኪስ ቀን መቁጠሪያዎች ተዘጋጅተውና ታትመው ለሚመለከታቸው መ/ቤቶችና እንዲሁም ለመ/ቤቱ ሠራተኞች ተሰጥቷል፡፡
- በማስታወቂያ ሚኒስቴር በሚዘጋጀው ኢትዮጵያ ዓመታዊ መጽሐፍ ውስጥ የመ/ቤቱን የ1997 በጀት ዓመት እንቅስቃሴ በተመለከተ የሚወጣ ጽሑፍ ተዘጋጅቶ የተላከ ሲሆን፣ አዳዲሶቹን በማስኤና የሕዝብና ቤት ቆጠራ ኮሚሽን ማቋቋሚያ አዋጆች ተዘጋጅተው ለቅ/ጽ/ቤቶች እንዲደርሱ ተደርገዋል፡፡ መ/ቤቱ የሚያወጣቸውን ሪፖርቶች ይዘት የህትመት ጊዜና መሰል መረጃዎችን በሚመለከት ብሮሸር ተዘጋጅቶ ለመረጃ ተጠቃሚዎች በመሠራጨት ላይ ሲሆን የመ/ቤቱን ራዕይ፣ ተልዕኮ፣ አላማና ዋና ዋና ተግባራትን አካቶ የያዘ ብሮሸር በአማርኛና በእንግሊዝኛ ቋንቋ ተዘጋጅቶ ለመ/ቤቱ የበላይ ኃላፊዎች ቀርቧል፡፡

## 10 <u>የኦዲት አገልግሎት</u>

- በ1998 ዓ.ም ዘጠኝ ወራት ውስጥ የመ/ቤቱን ገንዘብ ቤትና የዕቃ ግምጃ ቤት ሐምሌ 1/1997 ዓ.ም በማሸግ የገንዘብ ቤቱ የምርምራ ሥራና እንዲሁም የዕቃ ግምጃ ቤቱ የአላቂ ንብረቶች ቆጠራ ተደርጎና ሪፖርቱ ተዘጋጅቶ ለሚመለከተው አካል ተላልፏል፡፡
- የመ/ቤቱ የየወሩ የሳጥን ወይም የካዝና ምርመራ ተካሂዶ ሪፖርቱ ለመ/ቤቱ የበላይ አካል የቀረበ ሲሆን፤ የዕቃ ግምጃ ቤት የቋሚ ንብረት ገቢና ወጪ ምርመራም ተካሄዷል፡፡ እንዲሁም የመ/ቤቱ የመኪና መለዋወጫ ዕቃ ግምጃ ቤት ቆጠራ ምርመራ ተካሄዶ ሪፖርቱ ቀርቧል፡፡

- ከሐምሌ ወር 1996 ዓ.ም እስከ ግንቦት 1997 ዓ.ም ያለው የ1997 ዓ.ም የገቢና ወጪ ሂሣብ ምርመራ ተደርጓል፡፡

- የመ/ቤቱን የሩብ ዓመት ሪፖርት ለገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ሚኒስቴር ወቅቱን ጠብቆ ለማቅረብ የተቻለ ሲሆን፤ በዚህ ሪፖርት ውስጥ የመጽሐፍ ቆጠራና ምርመራ ለቅ/ጽ/ቤቶች በባንክ የተላከ ገንዘብ ዝርዝር ምርመራ የቼክ ክፍያዎች ምርመራ ተካሄዷል፡፡ የ1997 በጀት ዓመት ሂሣብ ዝርዝር ምርመራ የተጠናቀቀ ሲሆን፣ የ1998 በጀት ዓመት እስከ ህዳር ወር 1998 ያለው ዝርዝር የሂሣብ ምርመራም ተካሄዷል፡፡

## 11. ሕግ አገልግሎት

- መ/ቤቱ ለትምህርት ወደ ውጪ አገርና በአገር ወስጥ ልኳቸው ትምህርታቸውን አጠናቀው ሲመለሱ በገቡት ግዴታ መሠረት መ/ቤቱን ባለማገልገላቸው ምክንያት ሳይሠሩ የተከፈላቸውን ደመወዝ እንዲከፍሉ ለማድረግ በፍርድ ቤት የብር 20,823.47 ክስ በመመስረት በተደረገው ክትትል ብር 11,457.07 ገቢ የተደረገ ሲሆን፤ ቀሪው ብር 9,366.40 ክትትል እየተደረገበት ይገኛል፡፡

- የአፍሪካ ኢንሹራንስ በፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ያቀረበው የብር 5,649.98 እና አንድ ግለሰብ ያቀረቡት የብር 42,960 የይገባኛል የጉዳት ካሳ ክስ ክትትል እየተደረገበት ያለ ሲሆን፣ በሌላ በኩል ሁለት ግለሰቦች ያጉደለትን የመንግሥት ገንዘብ እንዲከፍሉ በቀረበው የብር 84,111.42 ክስ እስካሁን በተደረገው ክትትል ብር 11,395.00 ገቢ የተደረገ ሲሆን የብር 72,716.33 ክስ በቀጠሮ ላይ ይገኛል፡፡

- እንዲሁም ሁለት የመ/ቤቱ ሠራተኞች በሲቪል ሰርቪስ ኮሚሽን አስተዳደር ፍ/ቤት በመ/ቤቱ ላይ ያቀረቡት የይገባኝ ክስ አንደኛውን የዲሲፕሊን ኮሚቴው በድጋሚ ተመልክቶ ውሳኔ እንዲሰጥበት ያለ ሲሆን፤ ሁለተኛውን ይግባኝ የዲሲፕሊን ኮሚቴው ውሳኔ ትክክል አይደለም በማለት ሽሮታል፡፡

## 12. ፕላንና ፕሮግራም አገልግሎት

- በ1998 በጀት ዓመት መ/ቤቱ ለሚያካሂዳቸው ሁለት ፕሮጀክቶች ማስፈፀሚያ ከመንግሥት የተፈቀደውን ካፒታል በጀት ከሚመለከታቸው መምሪያዎችና አገልግሎቶች ጋር በመሆን በወርሃዊ የሥራ መርሃ ግብሩ መሠረት ወርሃዊ የገንዘብ ፍላጐት አዘጋጅቶ ለሚመለከተው ክፍል እንዲተላለፍ ተደርጓል።

- የ1998 በጀት ዓመት የስታቲስቲክስ የሥራ ዕቅድን በተፈቀደው በጀት መጠን አስተካክሎ ለመ/ቤቱ የበላይ አካልና ለሁሉም መምሪያዎችና አገልግሎቶች ለክትትል እንዲያመች አዘጋጅቷል።

- የኤጀንሲውን የመጀመሪያ ሩብ ዓመትና የስድስት ወራት ሪፖርት በማጠናቀርና በማዘጋጀት ለሚመለከታቸው ክፍሎች እንዲደርስ አድርጓል።

- የ1999 በጀት ዓመት የተቀናጀ ሰርቬይ ፕሮግራም እና የሦስተኛ ዙር የሕዝብና ቤቶች ቆጠራ ፕሮግራም ማስፈፀሚያ የካፒታል በጀት ፍላጐት የሚገልጽ የፕሮጀክት ዶክመንት ከሚመለከታቸው መምሪያዎችና አገልግሎቶች ጋር በመሆን አዘጋጅቶ ለመንግሥት አቅርቧል።

## 13. የአስተዳደርና ፋይናንስ አገልግሎት

### 13.1 የሰው ኃይል

በ1998 በጀት ዓመት መጀመሪያ ላይ በኤጀንሲው መ/ቤት 1,538 ቋሚና 2,339 የኮንትራት በጠቅላላው 3,877 ሠራተኞች ነበሩ። በዚህ ዘጠኝ ወራት ውስጥ ከቋሚ ሠራተኞች መካከል 30 በራሳቸው ፈቃድ የለቀቁ ሲሆን፣ ሦስት በዲስፕሊን ጉድለት ከሥራ ተሰናብተዋል። እንዲሁም ሁለት በጡረታ የተገለሉ ሲሆን፣ 19 በሞት ተለይተዋል። በአንጻሩም የ56 አዲስ ሠራተኞች ቅጥር ሲፈጸም 119 በዝውውር እንዲሁም አምስት ደግሞ በመንግሥት ትዕዛዝ ወደ መ/ቤቱ እንዲመለሱ ተደርጓል። በሌላ በኩል 2,844 የኮንትራት ሠራተኞች ከመ/ቤቱ ሲሰናበቱ 72 ሹፌሮች፣ 24 የሂሳብ ሠራተኞች፣ 4,233 ጀማሪ መረጃ

ሰብሳቢዎች፣ 66 ዳታ ኢንትሪ ኦፕሬተሮች፣ 84 ጀማሪ ስታቲስቲሽያንና ረዳት ካርታ ተቆጣጣሪዎች ቅጥር ተፈጽሟል።

በዚህም መሠረት በ1998 የዕቅድ ዘመን ዘጠኝ ወራት መጨረሻ ላይ ያለው ጠቅላላ የሰው ኃይል 5,643 ሲሆን ከዚህ ውስጥ 1,664 ቋሚና 3,979 የኮንትራት ሠራተኞች ናቸው።

ሠንጠረዥ 2 <u>የሰው ኃይል ሁኔታ</u>

| ተቁ | አጠቃላይ ሁኔታ | የሠራተኛ ቅጥር ሁኔታ | | |
|---|---|---|---|---|
| | | ቋሚ | ኮንትራት | ድምር |
| 1 | በበጀት ዓመቱ መጀመሪያ የነበሩ | 1,538 | 2,339 | 3,877 |
| 2 | አዲስ የተቀጠሩ | 56 | 4,484 | 4,540 |
| 3 | በመንግሥት ትዕዛዝ ወደ ሥራ የተመለሱ | 5 | - | 5 |
| 4 | በዝውውር ወደ መ/ቤቱ የመጡ | 119 | - | 119 |
| 5 | በተለያዩ ምክንያት ሥራ የለቀቁ | (33) | (2,844) | (2,877) |
| 6 | በጡረታ የተለዩ | (2) | - | (2) |
| 7 | በሞት የተለዩ | (19) | - | (19) |
| 8 | አሁን በሥራ ላይ ያሉ | 1,664 | 3,979 | 5,643 |

ከዚህ በታች በሠንጠረዥ የተገለፀው የሰው ኃይል በአገልግሎት ዓይነት ሲተነተን ቋሚ ሠራተኞችን በሚመለከት 202 በፕሮፌሽናል 811 መለስተኛ ፕሮፌሽናል፣ ሲሆን 651 የአስተዳደርና የጽሕፈትና የጠቅላላ አገልግሎት ሠራተኞች ናቸው። ዝርዝሩ በሚቀጥለው ሠንጠረዥ ላይ ቀርቧል።

<u>የሠራተኞች ሁኔታ በሥራ መደብ</u>

ሠንጠረዥ 3

| ፆታ | ቋሚ | | | | ኮንትራት | | | | ጠቅላላ ድምር |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | ፕሮፌሽናል | መለስተኛ ፕሮፌሽናል | ድጋፍ ሰጪ | ድምር | ፕሮፌሽናል | መለስተኛ ፕሮፌሽናል | ድጋፍ ሰጪ | ድምር | |
| ወንድ | 175 | 716 | 366 | 1,257 | 118 | 2,835 | 183 | 3,136 | 4,393 |
| ሴት | 27 | 95 | 285 | 407 | | 717 | 126 | 843 | 1,250 |
| ድምር | 202 | 811 | 651 | 1,664 | 118 | 3552 | 309 | 3,979 | 5,643 |

## 13.2 የበጀት አጠቃቀም

ለ1998 በጀት ዓመት የኤጀንሲው መ/ቤት ከመንግሥት የተፈቀደለት የመደበኛ እና የካፒታል በጀት በጠቅላላው ብር 112,692,988 ነው። ከዚህ ውስጥ ብር 36,636,700 ለብሔራዊ የተቀናጀ ሰርቬይ ፕሮግራም ማስፈጸሚያ፣ ብር 58,959,388 ለሕዝብና ቤቶች ቆጠራ ፕሮጀክት ለካርታ ሥራ የቅድመ ዝግጅት የሚውል ሲሆን ብር 17,096,900 ለመደበኛ ሥራ ማስኬጃና ለደመወዝ ክፍያ የሚውል ነው።

### 13.2.1 የመደበኛ በጀት አጠቃቀም

በዕቅድ ዘመኑ ከተመደበው ብር 17,096,900 ውስጥ በዘጠኝ ወራት ውስጥ ማለትም ከሐምሌ 1/97 ዓ.ም እስከ መጋቢት 30/98 ዓ.ም ድረስ ብር 13,133,599 ከገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ሚኒስቴር ተጠይቆ ገቢ የተደረገ ሲሆን፤ ከዚህ ውስጥ ብር 11,738,093 ሥራ ላይ ውሏል። ሥራ ላይ ከዋለው ብር ውስጥ 10,695,138 (63%) ያህሉ ለደመወዝ የተከፈለ ሲሆን፤ ብር 1,042,955 (6%) ደግሞ ለሥራ ማስኬጃ የዋለ ነው። በጠቅላላው ሥራ ላይ የዋለው ገንዘብ ለመ/ቤቱ ከተፈቀደው ጋር ሲነፃፀር 69% እንደሆነ የሚያመለክት ሲሆን ከገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ሚኒስቴር ተጠይቆ ገቢ ከሆነው ጋር ሲነፃፀር ደግሞ 89% ነው።

**የመደበኛ በጀት አጠቃቀም**

ሠንጠረዥ 4

| የወጪ ርዕስ | ለዓመቱ የተመደበ በጀት | በበጀት ዓመቱ ከተፈቀደው ውስጥ ተጠይቆ የመጣ | ተጠይቆ ገቢ ከሆነው ውስጥ ሥራ ላይ የዋለ | አፈፃፀም በመቶኛ | |
|---|---|---|---|---|---|
| | | | | ከዘጠኝ ወሩ | ከዓመቱ |
| 01 | 02 | 03 | 04 | 05 | 06 |
| ደመወዝ | 14,745,500 | 11,244,242 | 10,695,138 | 95 | 73 |
| ሥራ ማስኬጃ | 2,351,400 | 1,889,357 | 1,042,955 | 55 | 44 |
| ድምር | 17,096,900 | 13,133,599 | 11,738,093 | 89 | 69 |

### 13.2.2 የካፒታል በጀት አጠቃቀም

በ1998 በጀት ዓመት ኤጀንሲው ለሚያካሄዳቸው ሁለት ፕሮጀክቶች በጠቅላላው ብር 95,596,088 ተፈቅዶለታል፡፡ ከዚህ ውስጥ ብር 36,636,700 ለብሔራዊ የተቀናጀ ሰርቬይ ፕሮግራም ማስፈጸሚያና ብር 58,959,388 ደግሞ በ1999 ዓ.ም ለሚካሄደው የሕዝብና ቤቶች ቆጠራ የቅድመ ዝግጅት ለካርታ ሥራ የሚውል ነው፡፡

በዚህም መሠረት የሁለቱን ፕሮጀክቶች የበጀት አጠቃቀም በተናጠል እንደሚከተለው ለማመልከት ተሞክሯል፡፡

#### ሀ. ለብሔራዊ የተቀናጀ ሰርቬይ ፕሮግራም

በ1998 በጀት ዓመት ለብሔራዊ የተቀናጀ ሰርቬይ ፕሮግራም ማስፈጸሚያ የተፈቀደው ብር 36,636,700 ሲሆን፤ ባለፉት ዘጠኝ ወራት ውስጥ ብር 32,499,937 ከገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ሚኒስቴር ተጠይቆ ገቢ ሆኖ ብር 25,689,636 ሥራ ላይ ውሏል፡፡ ሥራ ላይ የዋለው ገንዘብ ተጠይቆ በእጅ ከገባውና ለመ/ቤቱ ከተመደበው ጋር ሲነፃፀር አፈፃፀሙ በቅደም ተከተል 79% እና 70% እንደሆነ ያመለክታል፡፡

## የብሔራዊ የተቀናጀ ስርቬይ ፕሮግራም በጀት አጠቃቀም

ሠንጠረዥ 5

| የሒሣብ መደብ | ለ1998 በጀት ዓመት የተፈቀደ | ለበጀት ዓመቱ ከተፈቀደው ውስጥ ከገ/ኢ/ል ሚኒስቴር ተጠይቆ ገቢ የሆነ | ገቢ ከሆነው ውስጥ ሥራ ላይ የዋለው | አፈጻጸም በመቶኛ | |
|---|---|---|---|---|---|
| | | | | ከዘጠኝ ወሩ | ከዓመቱ |
| 6113 | 13,332,200 | 11,343,929 | 9,800,709 | 86 | 74 |
| 6114 | 3,340,200 | 2,724,600 | 1,252,037 | 46 | 37 |
| 6123 | 880,900 | 720,360 | 697,084 | 97 | 79 |
| 6211 | 366,200 | 366,200 | - | - | - |
| 6212 | 300,000 | 255,000 | 158,474 | 62 | 53 |
| 6213 | 350,000 | 350,000 | 52,421 | 15 | 15 |
| 6217 | 3,254,000 | 2,468,900 | 1,748,778 | 71 | 54 |
| 6231 | 8,700,000 | 8,529,448 | 7,743,939 | 91 | 89 |
| 6232 | 539,400 | 539,400 | 693,381 | 129 | 129 |
| 6241 | 3,221,000 | 3,071,100 | 2,231,448 | 73 | 69 |
| 6243 | 60,000 | 48,000 | 8,188 | 17 | 13 |
| 6252 | 642,700 | 583,300 | 499,331 | 86 | 78 |
| 6254 | 1,090,100 | 1,090,100 | 586,274 | 54 | 54 |
| 6257 | 40,000 | 30,200 | 29,570 | 98 | 74 |
| 6258 | 340,000 | 250,900 | 107,708 | 43 | 32 |
| 6259 | 55,000 | 41,500 | 54,310 | 131 | 99 |
| 6271 | 125,000 | 87,000 | 25,984 | 30 | 21 |
| ድምር | 36,636,700 | 32,499,937 | 25,689,636 | 79 | 70 |

ለ. ለቆጠራ ካርታ ሥራ ፕሮግራም

በ1999 ለሚካሄደው የሕዝብና ቤቶች ቆጠራ ፕሮጀክት ለቆጠራ ቦታ ካርታ ዝግጅት በ1998 በጀት ዓመት ብር 58,959,388 ከመንግሥት የተፈቀደ ሲሆን፣ ባለፋት ዘጠኝ ወራት ውስጥ ብር 49,167,330 ከገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ሚኒስቴር ተጠይቆ ገቢ ሆኖ ብር 41,914,506 ሥራ ላይ ውሏል:: ጥቅም ላይ የዋለው ገንዘብ ተጠይቆ ገቢ

ከሆነውና ለዓመቱ ከተፈቀደው ጋር ሲነፃፀር በቅደም ተከተል 85 እና 71 ከመቶው ያህሉን ነው።

<u>የቆጠራ ቦታ ካርታ ሥራ ፕሮግራም በጀት አጠቃቀም</u>

ሠንጠረዥ 5

| የሂሣብ መደብ | ለ1998 በጀት ዓመት የተፈቀደ | ለበጀት ዓመቱ ከተፈቀደው ውስጥ ከገ/ኢ/ል ሚኒስቴር ተጠይቆ ገቢ የሆነ | ገቢ ከሆነው ውስጥ ሥራ ላይ የዋለው | አፈጻጸም በመቶኛ | |
|---|---|---|---|---|---|
| | | | | ከዘጠኝ ወሩ | ከዓመቱ |
| 6113 | 5,777,200 | 4,236,658 | 2,942,521 | 69 | 51 |
| 6114 | 1,850,400 | 1,191,000 | 821,275 | 69 | 44 |
| 6123 | 315,000 | 220,500 | 68,191 | 31 | 22 |
| 6212 | 4,300,000 | 4,262,500 | 114,593 | 3 | 3 |
| 6213 | 100000 | 100,000 | 22,000 | 22 | 22 |
| 6217 | 3,400,000 | 2,338,800 | 1,138,042 | 49 | 33 |
| 6231 | 9,500,000 | 6,134,700 | 6,682,431 | 109 | 70 |
| 6232 | 200,000 | 187,000 | 162,827 | 87 | 81 |
| 6241 | 2,100,000 | 1,719,300 | 1,398,342 | 81 | 67 |
| 6243 | 180,000 | 114,200 | 30,550 | 27 | 17 |
| 6254 | 177,400 | 177,400 | 408 | 0.23 | 0.23 |
| 6258 | 130,000 | 100,000 | 76,812 | 77 | 59 |
| 6259 | 90,000 | 72,000 | 41,514 | 58 | 46 |
| 6311 | 30,839,388* | 28,313,272 | 28,415,000 | 100 | 92 |
| ድምር | 58,959,388 | 49,167,330 | 41,914,506 | 85 | 71 |

* ለተሽከርካሪ ግዥ ብር 13,750,000 መፈቀዱ ይታወቃል። ቀሪው ብር 17,089,388 ደግሞ ተገዝተው ለመጡት ተሽከርካሪዎች የታክስ ክፍያ በገ/ኢ/ል/ሚኒስቴር በኩል ስለተከፈለ ነው።

## 13.3 አገልግሎት ነክ የሆኑ ሥራዎች

### 13.3.1 ጠቅላላ አገልግሎት ዋና ክፍል

- በ1998 በጀት ዓመት በዋናው መ/ቤትና በስታቲስቲክስ ቅ/ጽ/ቤቶች የደንብ ልብስ የሚያስፈልጋቸውን የሠራተኛ ቁጥር በማጣራት የስም ዝርዝራቸው እንዲሰበሰብ ተደርጎ ጨረታ በጋዜጣ ወጥቶ አሸናፊው በጨረታ ኮሚቴ ተለይቶ ከአሸናፊው ጋር ውለታውን ለመዋዋል በሂደት ላይ ይገኛል፡፡

- በዕርዳታ የተላኩ 16 ፕሪንተሮች፣ 25 ኮምፒውተሮች፣ 26 የፎቶ ኮፒ ማሽኖች ገቢ ተደርገዋል፡፡ የዋናው መ/ቤት የንብረት ቆጠራ ተደርጎ ሪፖርቱ ቀርቧል፡፡

- የአንድ ዓመት የኮምፒውተር ፕሪንተር የጥገና ኮንትራት በግልጽ ጨረታ በጋዜጣ እንዲወጣ ተደርጎ አሸናፊውን የመለየት ሥራ በጨረታ ኮሚቴው ተከናውኖ ከአሸናፊው ጋር ውለታ ተፈጽሞ የጥገና ሥራው በመካሄድ ላይ ይገኛል፡፡

- የመ/ቤቱን የጽ/መሣሪያ የህትመት አላቂ ዕቃዎች ቋሚ ዕቃዎችና የካርቶግራፊ ዕቃዎችን ግዥ ለመፈጸም በግልጽ ጨረታ በአዲስ ዘመን ጋዜጣ ወጥቶ ተጫራቾች ከተሳተፉ በኋላ በጨረታ ኮሚቴው አሸናፊው ተለይቶ የተወሰኑ ዕቃዎች ተገዝተው ገቢ የተደረጉ ሲሆን ሌሎችም ጨረታ ወጥቶላቸው በጨረታ ኮሚቴው በኩል በመታየት ላይ ናቸው፡፡

- መ/ቤቱ የተጠቀመባቸውን የስልክ፣ የመብራት፣ የውሃ ፍጆታና የኢንተርኔት ክፍያዎችን በሚመለከት አስፈላጊውን መረጃ ቢሉን በማየት የብር 309,974 ክፍያ እንዲፈጸም ተደርጓል፡፡

- በመ/ቤቱ የሚገኙትን የመኪና መለዋወጫ ዕቃዎች መ/ቤቱ ሊጠቀምባቸው የሚችሉትንና የማይጠቀምባቸውን በመለየት በንብረት አወጋገድ መመሪያ መሠረት እንዲከናወን ለማድረግ ለሚመለከተው አካል በማሳሰቢያ ተጠይቆ ምላሹ ስለተገኘ ሥራውን ለማከናወን ቅድመ ዝግጅት እየተደረገ ነው፡፡

- በመ/ቤቱ ለረጅም ጊዜ አገልግሎት በሰጡና በአሁኑ ሰዓት ከአገልግሎት ውጭ የሆኑ ልዩ ልዩ የመረጃ ወረቀቶች በንብረት አስወጋጅ ኮሚቴ አማካኝነት በተወሰነው መሠረት እንዲወገድ የተደረገ ሲሆን፤ የ600 አሮጌ ጎማዎችን በመንግሥት ደንብ መሠረት የማስገወድ ሥራ ተካሄዷል፡፡

- የመ/ቤቱን የቢሮ ጥበት ለማቃለል የአስተዳደርና ፋይናንስ አገልግሎት የሚጠቀምበትን ህንጻ በመከፋፈል የተወሰኑ ሠራተኞችን ለማስተናገድ ጨረታ ወጥቶ አሸናፊውም ተለይቶና ሥራው ተጠናቆ ወንበርና ጠረጴዛ የመግጠም ሥራ ለማከናወን ከአሸናፊው ድርጅት ጋር ውለታ ለመዋዋል ቅድመ ዝግጅት እየተደረገ ነው፡፡

- የመ/ቤቱ ተሽከርካሪዎች የሚጠቀሙበት የጎማ ግዥ ለመፈጸም ጨረታ በጋዜጣ ወጥቶ ውጤቱ ከጨረታ ኮሚቴው እየተጠበቀ ነው፡፡ እንዲሁም የመ/ቤቱ የኤሌክትሪክ አውቶማቲክ ስዊች ችግር ስለነበረበት በሙብራት ኃይል በኩል እንዲቀየር የተደረገ ሲሆን የእስቶክ ካርድ ምዝገባዎች እየተካሄዱ ይገኛሉ፡፡

- መ/ቤቱ ባለው አነስተኛ ጋራዥ ውስጥ ያለውን የመሥሪያ ቦታ ጥበት ችግር ለመቅረፍ አንድ አነስተኛ የሥራ ቦታ /የሸራ መጠለያ/ ተዘጋጅቶ ለሥራ ብቁ እንዲሆን ተደርጓል፡፡

### 13.3.2 ትራንስፖርትና ጥገና ክፍል

- የመ/ቤቱ 59 ተሽከርካሪዎች በዋናው መ/ቤት ጋራዥ የጥገና ሥራ ተካሄዶ ወደ ሥራ ተሰማርተዋል፡፡ እንዲሁም 26 ተሽከርካሪዎች በኢንሹራንስ ተጠግነው ለሥራ ብቁ የሆኑ ሲሆን 5 ተሽከርካሪዎች በጥገና ላይ ይገኛሉ፡፡ 79 ተሽከርካሪዎች ዓመታዊ የደህንነት ምርመራ ተደርጎላቸው ወደ ምድብ ቦታቸው ተሰማርተዋል፡፡

- በጨረታ ኮሚቴ የተመረጡ የ6 ጋራዦች ውል ተፈጽሟል፡፡ እንዲሁም የ248 ተሽከርካሪዎች የኢንሹራንስ አገልግሎት እንዲያገኙ ከመድን ጋር የውል ዕድሳት የተፈጸመ ሲሆን 21 ተሽከርካሪዎች በመድን ድርጅት ጥገናና ዕድሳት ተደርጎላቸው ለስምሪት ብቁ ሆነዋል፡፡

- መ/ቤቱ ለገዛቸው 50 ቶዮታ ላንድ ክሩዘር መኪናዎች አዲስ የፊትና የኋላ ሠሌዳ እንዲለጠፍ ተደርጓል፡፡ ለዚህም ተግባር ብር 17,000 ወጪ ሆኗል፡፡

- 150 ተሽከርካሪዎችም በተለያዩ የደንበኞች ጋራዦች ጥገና ተደርጐላቸዋል፡፡

- ለ25ቱም የስታቲስቲክስ ቅ/ጽ/ቤቶች ስለተሽከርካሪዎች አያያዝና አጠቃቀምን በሚመለከተ መመሪያ ተዘጋጅቶ ተሠራጭቷል፤ የተሽከርካሪ የጥገና ሂደታቸውም ምርመራ በማካሄድ ተረጋግጧል፡፡

### 13.3.3 ሕትመት ዋና ክፍል

በበጀት ዓመቱ ዘጠኝ ወራት ውስጥ በጠቅላላው 40,799 ጥራዝ ባለ 9,102,558 ገጾች የተለያዩ የሕትመት ሥራዎች ለመ/ቤቱ የተለያዩ የሥራ ክፍሎች አገልግሎት ሰጥቷል፡፡

## 14. የዕቅድ አፈፃፀሙ ሂደት ያጋጠሙ ችግሮች

እያደገ የመጣውን የመረጃ ፍለጐት ለማሟላት እንዲቻል በየወቅቱ ቁጥራቸው በዛ ያለ ባለሙያዎች የሚቀጠር ሲሆን፤ ከዚህ በፊትም የተቀጠሩት ለሥራቸው ምቹ የሆነ ቢሮ ለማግኘት ከመ/ቤቱ አቅም በላይ እየሆነ መጥቷል፡፡ በተለይም ደግሞ የሕዝብና ቤት ቆጠራ ኮሚሽንን እንደገና ለማቋቋም በወጣው አዋጅ ቁጥር 449/97 መሠረት የማዕከላዊ ስታቲስቲክስ ኤጀንሲን የኮሚሽኑ ጽ/ቤት እንዲሆን የደነገገ ሲሆን፤ በጽ/ቤቱ የሚሠሩ ባለሙያዎችና ድጋፍ ሰጪ ሠራተኞችን ተረክቦ በማሰራት ላይ ነው፡፡ ሆኖም በአንድ አካባቢ አድረጐ ለማሠራት በቂ የሥራ ቦታ ባለመገኘቱ በሁለት ቦታዎች ሆነው ሥራቸውን እንዲሠሩ እየተደረገ ይገኛል፡፡ ይህ ደግሞ በአጠቃላይ የኤጀንሲው ሥራ ላይ ተፅዕኖ ይኖረዋል፡፡

ይህም በመሆኑ በርካታ የሥራ ኃላፊዎችና ኤክስፐርቶቻቸው ተራርቀው የሚሠሩበት እንዲሁም አንድ ክፍል ከአቅም በላይ የሆነ የሰው ብዛት እንዲይዝ

በማድረጋችን ቢሮዎቻችን ለሠራተኞች የተመቹ የሥራ ቦታ ሲሆኑ ባለመቻላቸው የሠራተኞች የሥራ ተነሣሽነት እየቀነሰ የሚመጣበት ሁኔታን እየፈጠረ ይገኛል። በተጨማሪም ከፍተኛ የመንግሥት ሀብት የወጣባቸው የተለያዩ የመስክ መገልገያ ዕቃዎች በተለያዩ ጊዜያት መረጃ የተሰበሰበባቸው የጥናት ዶክመንቶችና ሌሎች ቁሣቁሶች አመች የሆነ ማከማቻ መጋዘን ባለማግኘታቸው ችግሩን የተደራረበ አድርጎታል። እንዲሁም በመላው አገሪቱ የተከፈቱ የስታቲስቲክስ ቅ/ጽ/ቤቶች ላይ ተመሣሣይ የሆነ የቢሮና የመጋዘን ችግር ያለባቸው ሲሆን፤ በዓመት መንግሥት ለዋና መ/ቤትና ለቅ/ጽ/ቤቶቹ ከግማሽ ሚሊዮን ብር በላይ ለኪራይ ወጪ ያደርጋል። በመሆኑም ለዋናው መ/ቤትና ለቅ/ጽ/ቤቶቻችን ለሥራ አመቺ የሆነ ቢሮ ለማግኘት እንድንችል ህንፃዎቹ የሚገነቡበት መንገድ እንዲመቻች እንጠይቃለን።